# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 002 መስከረም 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## «በመዲናዋ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶች የጎብኚዎችን ፍሰት በመጨመር የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ናቸው»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የተገነቡና እየተገነቡ የሚገኙት ሜጋ ፕሮጀክቶች የውጭ ጎብኚዎችን ፍሰት በመጨመር የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡

ከንቲባ አዳነች ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ እንደ ዓድዋ ሙዚየም ያሉ ከተማዋ ላይ እየተገነቡ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራትን ጎብኚዎች ፍሰት በመጨመር ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኙ ናቸው፡፡ እነዚህን ለትውልድ የሚተላለፉ ዐሻራዎችን ገንብቶ ለታለመላቸው ዓላማ ለማዋል ሌት ተቀን መሥራት ይገባል፡፡


እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ ፕሮጀክቶቹ የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚያሳልጡ ናቸው፡፡ የዓድዋ ሙዚየም ፕሮጀክት ነገ የሚፈጥረው ብቻ ሳይሆን ዛሬ የፈጠረውም የሥራ ዕድል በኢኮኖሚው ውስጥ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ወደፊትም ትልቁ የመስህብ ማዕከል ሆኖ እንደሚያገለግል ጥርጣሬ የለንም ፡፡

አዲስ አበባ መበልጸግ ይገባታል፡፡ የዜጎቿም ሕይወት

« በመዲናዋ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "ታሪክን መሰረት ባደረጉ ብዥታዎች ላይ ትውልዱን ማወያየት ይገባል"

- ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ
የታሪክ ተመራማሪ



**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ታሪክን መሰረት ያደረጉ ብዥታዎች እንደሀገር ችግር እየፈጠሩ በመሆኑ ትውልዱ ቀጣይነት ባለው መልኩ ስለኢትዮጵያ እንዲወያይ ማድረግ ይገባል ሲሉ የታሪክ ተመራማሪው ባህሩ ዘውዴ (ኤመሬተስ ፕሮፌሰር) አስታወቁ።

ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንደገለጹት፤ ትውልዱን ስለኢትዮጵያ ጉዳይ ይበልጥ እንዲመካከር በማድረግ ታሪክን መሰረት ያደረጉ ብዥታዎች ይበልጥ ችግር እንዳይፈጥሩ መስራት ይገባል።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በተመለከቱ ጉዳዮች

"ታሪክን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በአዲሱ ዓመት አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ ለማስገባት እየተሰራ ነው

- ከ300 በላይ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ለማልማት ፍላጎት አሳይተዋል
- ወደ ውጭ ከተላኩ አግሮ ኢንዱስትሪ ምርቶች 40 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ በ2016 ዓ.ም አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ እንዲገቡ እየተሰራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ከ30 በላይ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ለማልማት ፍላጎት ማሳየታቸውን የተገለጸ ሲሆን ወደ ውጭ ከተላኩ የአገሮ ኢንዱስትሪ ምርቶች 40 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱም ተጠቁሟል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ቡልቡላ፣ ይርጋለም እና ቡሬ ላይ የሚገኙት የተቀናጁ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታቸው ከ90 ፐርሰንት በላይ ተጠናቆ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ ፓርኮቹን ሙሉ ለሙሉ ወደ ስራ ለማስገባት

በአዲሱ ዓመት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል















## «ኢትዮጵያውያን በየሕይወታቸው ምዕራፍ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ታሪክ መጻፍ ይገባቸዋል»

- ዶክተር ሮዳስ ታደሰ
የጥንታዊ መዛግብት ተመራማሪና ፀሃፊ

ገጽ 4







ዜና

# የመዲናዋ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ይጠናቀቃል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአንድ ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ምትኩ አስማረ እንደገለጹት፤ አንድ ቢሊዮን ብር ወጪ ግንባታው እየተካሄደ የሚገኘው የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል በቀጣይ 11 ወራት ተጠናቆ የሙከራ ሥራዎች ተደርገውለት ወደ ሥራ ይገባል።

እንደ አቶ ምትኩ ገለጻ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከል በሦስት ሺህ ካሬ ሜት መሬት ላይ ያረፈ ነው።

የትራፊክ መቆጣጠሪያ ማዕከሉ ሲጠናቀቅ የአዲስ አበባን የትራፊክ ፍሰት ለማስተካከል ይረዳል ያሉት አቶ ምትኩ፣ ማዕከሉ ቴክኖሎጂ የተሟላላቸው አራት ሰፋፊ ክፍሎች አሉት ብለዋል።

በማዕከሉ ሲጠናቀቅ አጠቃላይ የትራፊክ ሥርዓቱን ከአንድ ማዕከል መቆጣጠር እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ በተለይም በከተማው የሚደረጉ የትራፊክ ቁጥጥሮችን ለማካሄድ ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማዋ የትራፊክ መጨናነቅ የሚታየው መብራቶች አካባቢ በመሆኑ ከአንድ ቦታ ላይ ለመቆጣጠር የሚስችል ማዕከል መሆኑን ገልጸዋል።

መዲናዋ የተለያዩ ሀገር፣ አህጉርና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ለማዘጋጀት የሚያስችል የመንገዶችን ቁጥጥርን በማዕከሉ እንደሚካሄድ የገለጹት አቶ ምትኩ፤ ተሽከርካሪዎችን ከትራፊክ ፍሰቱ ጋር በማመጣጠን ለመልቀቅ የሚያስችል ሥርዓት ያለው መሆኑን




አስረድተዋል።

ማዕከሉ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎች ከቢሮ ሆነው የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት ያለው መሆኑን በመግለጽ፣ በተለይም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተሽከርካሪዎችና የሚዘጉ መንገዶችን በመለየት የተሳለጠ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

ማዕከሉ ሲጠናቀቅ የተለያዩ ተቋማትን ቅንጅት ያሳድጋል ያሉት አቶ ምትኩ ፣የትራፊክ ፖሊስ፣ የማኔጅመንት ኤጀንሲ፣ የከተማ አውቶቡስ፣ እሳት አደጋን ጨምሮ ፖሊስና የደህንነት ኃይሎች በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

ሥርዓቱ ተግባራዊ ሲሆን የተሽከርካሪን ፍጥነት በ9 ነጥብ 7 በመቶ የሚያሳድግ መሆኑን ጠቅሰው፣ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የአውቶቡሶች የሚጓዙበትን ጊዜ 25 በመቶ ይቀንሳል ነው ያሉት።

በማዕከሉ በሚደረግ ክትትል አጥፊ አሽከርካሪዎችን በቀላሉ ለመለየት አስቻይ መሆኑን በመግለጽ፣ የአጥፊ አሽከርካሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

የትራፊክ ፍሰቱ መሳለጥ ዜጎች በሚፈልጓቸው ቦታዎች ላይ በፍጥነት እንዲደርሱ በማድረግ ምርታማነትን ለማሳደግ እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ተሽከርካሪዎች የሚያወጡትን የነዳጅ ወጪንና ለረዥም ጊዜ መቆምን የሚያስቀር መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ ሁንዴ በቀለ

# በቀጣዮቹ 10 ዓመታት በክልሉ 25 አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች ይገነባሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዳማ፡- በቀጣዮቹ 10 ዓመታት ውስጥ ደረጃቸውን የጠበቁ 25 አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለመገንባት አቅዶ እየሠራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው የ2015 ዓ.ም የእቅድ አፈጻጸሙንም ገምግሟል።

በወቅቱ በኦሮሚያ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ቢሮው በቀጣዮቹ 10 ዓመታት በክልሉ የቱሪዝም መስፈርትን የሚያሟሉ 25 አዳዲስ መዳረሻዎች ለመገንባት አቅዶ እየሰራ ይገኛል።

በክልሉ ያሉ የቱሪዝም መስህቦችን መሠረተ ልማት በማሟላት ወደ መዳረሻነት መቀየር እንደሚያስፈልግ የተናገሩት አቶ ሁንዴ፤ በቀጣይ የሚለሙት አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎቹ ወጪያቸው በመንግሥትና በባለሀብቶች እንደሚሸፈን አመልክተዋል።

አቶ ሁንዴ እንደገለጹት፤ ቱሪዝም ካለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተጨማሪ በዲፕሎማሲው ዘርፍ የሀገርን ገጽታ ከመገንባት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ እየተወጣ ይገኛል።

በ2015 ዓ.ም በክልሉ የቱሪስት መዳረሻዎችን በማስፋፋት ረገድ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ ሁንዴ፤ ከዘጠኝ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች በክልሉ የሚገኙ የቱሪስት ሥፍራዎችን መጎብኘታቸውን አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ ከአስር ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መገኘቱን ገልጸው፤ ገቢውን ለማሳደግ በቀጣይ የቱሪዝም ንቅናቄ ስራዎች እንደሚከናወኑ አስረድተዋል።

ከዚህ በፊት በርካታ መስህቦች የነበሩ ቢሆንም ወደ ቱሪስት መዳረሻነት የመቀየር ውስንነቶች እንደነበሩ ጠቁመዋል። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በዘርፉ ለ50 ሺህ ሰዎች የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ44 ሺህ ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል ያሉት አቶ ሁንዴ፤ በቀጣይም በዕቅድ የተያዙ የቱሪስት መዳረሻዎች ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ በመቶ ሺዎች ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚያስችሉ ተናግረዋል።

በተለይ የአደባባይ በዓላት የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማስፋት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው ፤ መጪው ኢሬቻ በዓል በሰፊው እንዲከበር ዝግጅት መጠናቀቁን ገልጸዋል። በኦሮሚያ የቱሪዝም ኮሚሽን ምክትል ኮምሽነር አቶ ደራራ ከተማ በበኩላቸው፤ ኮምሽኑ በክልሉ ያሉ መዳረሻዎችን ለማስፋት በቂ የማስተዋወቅ ሥራዎች ተሰርቷል ብለዋል።

በተለያዩ በክልሉ ከተሞች ቱሪዝምን የማስፋፋት እንዲሁም በቦረና ብሔራዊ ፓርክና በአቢያታ ሻላ ሐይቅ ውስጥ የተገነቡ ሎጆችን በመጠቀም የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር የተለያዩ ስራዎች መከናወናቸውን አስረድተዋል።

እንደ አቶ ደራራ ገለጻ፤ ክልሉ ሰፊ የቱሪዝም ሀብት ያለው ቢሆንም በበቂ መልኩ ባለመሰራቱ እንዲሁም ቱሪዝሙ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምንጭ ተደርጎ ባለመሰራቱ እንዲሁም የባለሙያዎች ችግር ባለው ልክ ጥቅም እንዳይገኝ አድርጓል።

# በከተማዋ በአሠራር ሥርዓት የታዩ ክፍተቶችን ማረም ላይ ትኩረት ይደረጋል

**መዓዛ ማሞ**




አዲስ አበባ፡- በሃዋሳ ከተማ በአሠራር ሥርዓቱ የታዩ ክፍተቶችን ማረም ላይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራ የከተማ አስተዳደሩ ገለጸ።

የከተማዋ ምክትል ከንቲባ አቶ መኩሪያ መርሻዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሲዳማ ክልል ባለፉት ሶስት ዓመታት ህዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። በቅርቡ በተደረገው ግምገማ በከተማዋ ጎልተው በድክመት የታዩና መታረም ያለባቸው ጉዳዮች ላይ በቀጣይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።

በክልል ደረጃ በሃዋሳ ከተማ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ተብለው የታመኑባቸው ጉዳዮች በተለይ ከአሠራር ጋር የተያያዙ ችግሮች በመሆናቸው ገልጸው፣ እነዚህን የከተማዋን ችግሮቹን ለመቅረፍ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

የፕሮጀክት አፈጻጸም የአስተዳደር ሥርዓቱ የግልጸኝነት ችግር የታየበትና ቅድሚያ መሰጠት ለሚገባው ቅድሚያ ያልሰጠ በመሆኑ አቶ መኩሪያ አውስተው፤ ፕሮጀክቶች ሲሠሩ ህብረተሰቡን አስቀድሞ ማነጋገር እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት ።

ምክትል ከንቲባው ከአራትና አምስት ዓመታት በፊት የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ከማስጨረስ ይልቅ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን መጀመር ላይ ማዘንበሉ ችግር ፈጥሮ መቆቱን ተናግረዋል። የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ችግሮችን ለይቶ ማጠናቀቅ የሚያስፈልግ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራበት አመልክተዋል።

የፋይናንስ ሥርዓቱ ግልጸኝነትን እንደሚፈልግ የሚናገሩት ምክትል ከንቲባው፣ በመደበኛና በሴፍቲኔት ፕሮግራም የታዩ የግልጸኝነት ክፍተቶችን በማረም በቀጣይ የፋይናንስ ሥርዓቱ ግልጸኝነት ላይ ትኩረት ይደረጋል ብለዋል።

አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ህብረተሰቡ ከከንቲባ ጀምሮ እንደሚያማርር የተናገሩት አቶ መኩሪያ፣ ከንቲባው የህዝብ አገልጋይ በመሆኑ በከንቲባ ደረጃ ለሚፈታ ጉዳይ ጊዜ ሰጥቶ በማዳመጥ ችግሮችን ለመፍታት በቅርበት ይሰራል ብለዋል። አደረጃጀቱ ከቀበሌ ጀምሮ ሁሉም በየደረጃው የሚፈቱ ጉዳዮችን በመፍታት የነበሩ ክፍተቶችን በማረም ረገድ ትኩረት እንደሚደረግም ተናግረዋል።

ማዘጋጃ ቤትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አካባቢ የነበረው አሠራር ለውጥ የሚፈልግ በመሆኑ ሕብረተሰቡ ለሚያነሳው የአገልግሎት አሰጣጥ ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት አኳያ ሥራዎች እንደሚሰሩ አስረድተዋል። የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በመፍታትና በማዘመን ላይ በኃላፊነት እንደሚሠራም አክለው ገልጸዋል።

የማስፋፊያ ሥራዎች የመንገድ ከፈታ፣ የመሠረተ ልማት፣ ውሃና ኤሌክትሪክ ሃይል ሕብረተሰቡ ከሚያነሳቸው ችግሮች መካከል በመሆናቸው በቀጣይ በትኩረት ይሠራባቸዋል ብለዋል። ከተማው ማዕከል አካባቢ ውብ መሆኑን የሚናገሩት አቶ መኩሪያ፣ ሌሎች አካባቢዎችን በተመሳሳይ ለማስዋብ የሶስት ወር ዕቅድ ለማዘጋጀት ግብዓት እየተሰባሰበ መሆኑን አስረድተዋል።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደታች በመውረድ በየቀበሌው ህዝቡን የማወያየት ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመው፣ የህዝቡን ሃሳብ አዳምጦ በተገኘው ግብዓት በቅደም ተከተል የሚፈቱ ጉዳዮች ተለይተው በተለየ እቅድ እንደሚተገበሩ ተናግረዋል።

አጠቃላይ በሃዋሳ ከተማ የሪፎርም ሥራ መሠራቱን የተናገሩት አቶ መኩሪያ፣ ከንቲባን ጨምሮ 12 የሚሆኑ የመምሪያ ኃላፊዎች በአዲስ መተካታቸውን ተናግረዋል።

የከተማው ካቢኔ ባደረገው የመጀመሪያ ስብሰባም የገቢ አሰባሰቡ ፣የጸጥታ ሥራና ያለውን ሰላም በማስቀጠል የተለየ ትኩረት አድርጎ ለመስራት አቅጣጫ መቀመጡን አስረድተዋል።

መሠረተ ልማት ላይ የጎርፍ ችግሮችን ለመቅረፍ በአጭር ጊዜ ተጠንቶ እልባት እንዲያገኝ እንደሚሠራ የገለጹት አቶ መኩሪያ፣ ሃዋሳ ከተማ የምትታወቅበትን የቱሪዝም ዘርፍም ትኩረት ተሰጥቶ ከሚሠራባቸው ጉዳዮች አንዱ መሆኑን አስረድተዋል።

# በተማሪዎች ሰርቪስ ላይ የተደረገው የ150 በመቶ ጭማሪ አግባብ አለመሆኑን ወላጆች ቅሬታ አቀረቡ

## - የዋጋ ጭማሪው ሚዛናዊነትን የጠበቀ ነው ሲል ድርጅቱ ገልጿል

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በተማሪዎች ሰርቪስ (ስኩል ባስ) ላይ የ 150 በመቶ ጭማሪ መደረጉ ተገቢ ያልሆነና አቅማችንን ያላገናዘበ ነው ሲሉ የተማሪ ወላጆች ቅሬታ አቀረቡ። የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት በበኩሉ፤ የዋጋ ጭማሪው ሚዛናዊነትን የጠበቀ እንጂ ከወላጆች የተለየ ትርፍ ለማግኘት የተደረገ አይደለም ሲል ምላሽ ሰጥቷል።

በስኩል ባስ አማካኝነት ተማሪ ልጃቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንደሚወስዱ የተናገሩት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ አቶ ተስፋዬ ገረመው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም የጉዞ ርቀቱ እስከ ሰባት ኪሎ ሜትር ድረስ ለሆነ ትምህርት ቤት በአንድ ተማሪ 500 ብር የሰርቪስ አገልግሎት ክፍያ ስንከፍል ቆይተናል።

በአሁኑ ጊዜ በማናውቀው ምክንያት ለአንድ ተማሪ አንድ ሺህ 250 ብር እንድንከፍል ተጠይቀናል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

እኔንም ጨምሮ ሌሎች የተማሪ ወላጆች የካቲት 2015 ዓ.ም ስብሰባ ተጠርተን ነበር ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በስብሰባው ላይ ከ2016 ጀምሮ የጉዞ ርቀቱ እስከ ሰባት ኪሎ ሜትር ድረስ ለሚጓዝ አንድ ተማሪ 750 ብር እንደሚከፈል ተወስኖ እንደነበር ገልጸዋል።

አሁን ግን ይህ ውሳኔ ተቀልብሶ የ 150 በመቶ ጭማሪ ለምን ተደረገ ብለን ጥያቄ ብናቀርብም ምላሽ የሚሰጠን አካል አላገኘንም ሲሉ አቶ ተስፋዬ ተናግረዋል።

አንዴ ስለተወሰነ መክፈል የምትችሉ መጥታችሁ ውላችሁን አድሱ፤ ካላደሳችሁ ግን አናስተናግዳቹሁም የሚል ምላሽ በማስታወቂያ እንደተለጠፈ አስረድተዋል።

ሌላኛዋ ቅሬታ አቅራቢ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪና የተማሪ ወላጅ ወይዘሮ ሕይወት በቀለ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በሀገርና በግለሰብ ደረጃ ያለው የኑሮ ውድነት መፍትሄ ባላገኘበት ሁኔታ በተማሪዎች ሰርቪስ ላይ የተጋነነ የዋጋ ጭማሪ ማድረጉ ተገቢ አይደለም ብለዋል።

አውቶቡስ አገልግሎቱ ልጆቻችን ደህንነታቸው ተጠብቆ በጊዜ በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲገኙ በማድረግ ረገድ የሰርቪስ አገልግሎት መልካም መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ ሕይወት፤ የተደረገው የዋጋ ጭማሪ ግን ፍትሃዊ ያልሆነና ኑሮአችን ላይ ጫና የሚያሳድር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አዳነ አብደታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ምላሽ፤ በተማሪዎች የሰርቪስ አገልግሎቱ ላይ የተደረገው የዋጋ ጭማሪ ወቅቱንና ሚዛናዊነትን የጠበቀ እንጂ ከወላጆች የተለየ ትርፍ ለማግኘት ታስቦ የተደረገ አይደለም ብለዋል።

ድርጅቱ ለተከታታይ አምስት ዓመታት የተማሪ ሰርቪስ አገልግሎት ላይ ምንም አይነት የዋጋ ማሻሻያ ሳያደርግ አገልግሎት መስጠቱን የገለጹት አቶ አዳነ፤ ከተማሪ ወላጆች የሚሰበሰበው ገንዘብ የነዳጅ፣ የሹፌር ደመወዝና የተሽከርካሪ መለዋወጫ ወጪዎችን የሚሸፍን አለመሆኑን አመላክተዋል።

ዛሬ ላይ ያለው የነዳጅና የመለዋወጫ ዕቃ ዋጋ ጨምሯል ያሉት አቶ አዳነ፤ ድርጅቱ ጊዜ ወስዶ ጥናት በማድረግ የዋጋ ማሻሻያውን ማድረጉን አስታውቀዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ለመደበኛው ትራንስፖርት እንጂ በተለየ መልኩ ለተማሪ ሰርቪስ አገልግሎት የሚውል ድጎማ እንደማያደርግ ጠቁመው፤ ወቅቱን ያገናዘበ ጭማሪ በመደረጉ ወላጆች ቅሬታ ሊሰማቸው እንደማይገባ አስረድተዋል።

ድርጅቱ የተማሪ ሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ መጠን ያላቸው 100 አውቶብሶች እንዳሉት የጠቆሙት አቶ ተስፋዬ፤ አሁን ላይ 82 አውቶብሶች አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛል ብለዋል።

# ክልሉ

## ለሁስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች የስራ ዕድል ፈጥሯል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠሩን የኦሮሚያ ክልል የሥራ ዕድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ ገለጸ።

የቢሮው ምክትል ኃላፊና የስልጠና ዘርፍ ኃላፊ አቶ አደም ከማል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ እንደገለጹት በክልሉ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል አግኝተዋል።

በሥራ እድል ፈጠራ የግብርናው ዘርፍ ሰፊውን ድርሻ እንደሚወስድ የተናገሩት አቶ አደም፤ እስከ 70 በመቶ የክልሉን የስራ ዕድል ፈጠራ በግብርናው ዘርፍ እንደተሸፈነ አስረድተዋል።

በተጨማሪ በአገልግሎት ዘርፍ የተሻለ የስራ ዕድል መፈጠሩን ገልጸው፤ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ዘርፎች ተጨማሪ የስራ ዕድል የተፈጠረባቸው ዘርፎች መሆናቸውን አመልክተዋል።

በበጀት ዓመቱ ለስራ ዕድል ፈጠራ ከአራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ብድር የተሰጠ ቢሆንም፤ ገንዘቡ በሰው ቁጥር ሲካፈል ዝቅተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ተሳትፎም አነስተኛ እንደሆነ ተናግረዋል።

የስራ ዕድል ፈጠራውን ውጤታማነት በተመለከተ ዝርዝር ግምገማ እየተካሄደ መሆኑን አስረድተዋል።

ከመስከረም ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ ምን ያህል ኢንተርፕራይዞች ወደ ስራ የገቡት፤ ምን አይነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ፤ ክፍተታቸው ምንድነው የሚሉ ጉዳዮችን በግምገማው እየተዳሰሱ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ ዜጎች ያላቸውን ክህሎት ተጠቅመው ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



አቶ አደም ከማል

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ለሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በተለያዩ ዘርፎች ስልጠና መስጠቱን አስታውቀዋል።

ከ180 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች ስልጠና መውሰዳቸውን ምክትል ኃላፊው ተናግረው፤ ከእነዚህ መካከል 126 ሺህ የሚሆኑት ወደ ስራ መግባታቸው ተናግረዋል። በስልጠናው በሀገሪቱ ያሉትን የክህሎት ክፍተቶች በመገምገም ውጤታማ የስራ ዕድል ፈጠራን ለማበረታታት ያግዛል ብለዋል።

አቶ አደም እንደገለጹት፤ በክልሉ አሁንም በግብርናውና በማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፎች ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል አቅም አለ። ይህን አቅም ወደ ስራ ለመለወጥ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ይበልጥ መስራት ይኖርበታል።

# “ለዩኒቨርሲቲ መግቢያና መውጫ ፈተና የተሰጠው ትኩረት ለመማር ማስተማር ሂደቱም ሊሰጥ ይገባል”

- አማኑኤል ኤሮሞ (ዶ/ር)
የትምህርት አመራርና አስተዳደር መምህር

**ታደሰ ብናልፈው**



አዲስ አበባ፡- የትምህርት ጥራትን ለማምጣት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመውጫና የመግቢያ ፈተና ጥብቅ ቁጥጥር በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ሊተገበር እንደሚገባ የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት አመራርና አስተዳደር መምህር አማኑኤል ኤሮሞ (ዶ/ር) ገለጹ።

ዶክተር አማኑኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለመግቢያና ለመውጫ ፈተና እየተሰጠ ያለው ጥብቅ ቁጥጥር የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ከፍተኛ ጥቅም አለው። የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መግቢያና መውጫ ፈተና እየተሰጠ ያለው ትኩረት ለመማር ማስተማር ሂደቱ ሊሰጥ ይገባል።

መንግሥት እየተከተለ ያለው የዩኒቨርሲቲ የመግቢያና የመውጫ ፈተና ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የፈተና ስርቆትን ማስቀረት የቻለ ከመሆኑ ባለፈ ተማሪዎች በራሳቸው ብቃትና ጥረት የከፍተኛ ትምህርትና የስራውን ዓለም እንዲቀላቀሉ ማድረግ የሚችል ነው፤ ይህም በሂደት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የራሱን አስተዋጽኦ ይጫወታል ብለዋል።

የሀገሪቱን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የታየውን የፈተና ቁጥጥርና ጠንካራ ስራ በመማር ማስተማሩ፣ በሥርዓተ ትምህርት ተገቢነት፣ በአመራሩ ብቃት፣ በአስተማሪው የማስተማር ብቃትና ቁርጠኝነት፣ በተማሪው ዝግጁነትና ተሳትፎ እንዲሁም በትምህርት ግብዓት አቅርቦት መሟላት ላይ ሊተገበር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር አማኑኤል ገለጻ፤ ፈተና ተማሪዎች ራሳቸውን ምን ያህል እንደሰሩ የሚገመግሙበት የመፈተሻ መንገድ እንጂ ብቻውን የትምህርት ጥራት ማምጣት አይችልም፤ የትምህርት ሁለተናዊ ጥራትን ለማምጣት የመማር በማስተማር ሂደቱ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት ይገባል ።

የትምህርት ጥራት መጣ የሚባለው ተማሪው አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች ሲፈጥርና ሲያመነጭ፣ የቴክኖሎጂን ማሰጋገርና መተንተን ሲችል፤ ችግር የሚፈቱ ምርምሮችንና ጥናቶችን በመስራት ተግባራዊ ለውጥ ማምጣት ሲችል ነው ያሉት ዶክተሩ፤ ይህንን ለውጥ ለማምጣት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል።

የሀገር ሁለንተናዊ ለውጥ የሚረጋገጠው በትምህርት በመሆኑ የትምህርት ጥራት የሁልጊዜም አጀንዳ ሊሆን ይገባል፤ ምሁራን ጥናቶችንና ምርምሮች በመስራት በፈተና የታየውን ቁጥጥርና ክትትል በመማር ማስተማሩ ሂደቱ ላይ እንዲተገበር በመግባባት መስራት አለባቸው ሲሉ ጠቁመዋል።

የመምህሩ የማስተማር ብቃትና ተነሳሽነትና የተማሪው የመማር ፍላጎትና ዝግጁነት፣ የአስተዳደርና የአመራር ብቃት የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ቁልፍ መፍትሔ ናቸውም ብለዋል።

መንግሥት በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመግቢያና የመውጫ ፈተና ጥራት ያሳየውን ቁርጠኝነት ትምህርትን ከፖለቲካ ነፃ በማድረግ ህጎችንና ፖሊሲዎችን አውጥቶ ተጠያቂነትን በማረጋገጥ በመማር ማስተማሩን የተሳለጠ ማድረግ እንደሚገባው ጠቁመው፤ የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ማህብረሰቡ ከትምህርት ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት አለባቸው ሲሉም አመልክተዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያውያን በየሕይወታቸው ምዕራፍ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ታሪክ መጻፍ ይገባቸዋል››

- ዶክተር ሮዳስ ታደሰ
የጥንታዊ መዛግብት ተመራማሪና ፀሃፊ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን በእያንዳንዱ የሕይወታቸው ምዕራፍና በ365 እያንዳንዱ ቀናት ሽክርክሪት ለሀገር፣ ለወገንና ለዓለም የሚጠቅም ታሪክ ሊጽፉ እንደሚገባ የጥንታዊ መዛግብት ተመራማሪ እና ጸሃፊ ዶክተር ሮዳስ ታደሰ ገለጹ።

ዶ/ር ሮዳስ አዲሱን ዓመት አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘመን ኡደት፣ ሽክርክሪት ጉዞ ነው። በዘመን አንቆምም እንሄዳለን። ሁሉም ተንቀሳቃሽ ነው። ጸሃይ፣ ጨረቃም ይንቀሳቀሳል። በስራና በሕይወት ለውጥ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል።

አዲስ ዓመት አዲስ ማንነት ይዘን የምንጓዝበት ነው ያሉት ዶ/ር ሮዳስ፤ ከኡደት ጋር አብረን መሄድ አለብን። አምላክ በየዓመቱ 365 ገጽ ያለበት ምንም ያልተጻፈበት ንጹህ ወረቀት ሰጥቶናል። በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የወደድነውን እንድንጽፍበት ተፈቅዷል። በእነዚህ ቀናቶች ሀገር፣ ወገንና ዓለምን የሚጠቅምና የሚያኮራ ስራ ልንሰራበት ይገባል ነው ያሉት።

ዘመን ለመቁጠር ለመስፈር፤ ጸሃይ፣ ጨረቃ ከዋክብት ያስፈልጋሉ። ለጸሃይ አቆጣጠር ካሌንደር መቀመር ይቻላል። በጨረቃ አቆጣጠር ዘመንን መቀመር እንደሚቻልም አመልክተዋል።

ጥንት ኢትዮጵያውያን ሰማይን፣ ጸሃይን፣ ከዋክብትንና ጨረቃን በአጠቃላይ ሰማያዊ አካላትን በመመርመራቸው ምክንያት ልዩ የዘመን አቆጣጠር ስርዓት ለመስራት እንደቻሉም ተናግረዋል።

በጸሃይ አቆጣጠር ሥርዓት ዛሬ 2016 ዓ.ም ላይ ገብተናል። ምክንያቱም አንድ ዓመት ኢትዮጵያውያን የዘመን ቀመር 365 ዕለት ከ15 ኬክሮስ ወይም 06 ካሊት ይባላል፤ ከ06 ሰዓት ከሁለት ደቂቃ እንደሆነም በምሳሌ አስረድተዋል።

በጨረቃ አቆጣጠርም 354 ዕለት ከ22 ኬክሮስ ከ01 ካሊት፣ ከ37 ሳልፊት ከ52 ራቢት ከ48 አምፊት እንደሚባል። አውዳመቷ የምትጨርስበት ወቅት መሆኑም ነው የገለጹት። ስለዚህ በጨረቃ አቆጣጠር 2077 ዓመተ ምህረት ላይ እንደተገባም ተናግረዋል።



ጸሃይን በመቀመር የጸሃይ ዘመን አቆጣጠር ካሌንደርን፣ በጨረቃ በመቀመር ደግሞ ሉናር ካሌንደርን በመስራታቸው ምክንያት በሁለቱም መቀመር የሚችል የዘመን አቆጣጠር እንዲኖር ማስቻሉን አመልክተዋል። የኢትዮጵያ የዘመን ቀመር ከምእራባውያኑ የዘመን ቀመር ጋር የሰባት ዓመት፣ የ 11 ዕለታት ልዩነት እንዳለውም ነው የጠቀሱት።

ኢትዮጵያውያን ጳጉሜን 13 ኛ የመጨረሻ ወር ሲኖረን እነርሱ ግን ጳጉሜን ስላጠፉ እያንዳንዱ ወራቸው 31፣ 30፣ አንድ ወር የካቲት 28 አላቸው። በኢትዮጵያ 30 ዕለታት አሉ፤ እነዚህ ነገሮች ብዙ ልዩነትን አስከትለዋል ብለዋል።

በመሰረታዊ ልዩነቱ የ 753 ዘመን ነበር። አሁን ተቀራርቦ ሰባት ዓመት ሆኗል። በተለይ ኢትዮጵያን ሌሎች በቤዛንታይን ግዛት የነበሩ ይከተሉት የነበረ የዘመን ቀመር ዓመተ ፍጥረት ወይም ዓመተ ዓለም የሚባል ነው።

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለውን ይቀምሩ ነበር። ከክርስቶስ ዘመን በፊት የነበረውን ዘመን ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ በማለት ይቀምሩ የነበሩት የሮም ከተማ የተመሰረተችበትን ቅድመ ልደተ ክርስቶስ 753 ዘመንን አንድ ብሎ በመቁጠር እንደነበረም ነው የጠቆሙት።

# በአዲሱ ዓመት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የማስተዋወቅ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸው በፓርኮቹ ገብተው ማምረት የጀመሩ ባለሀብቶች ወደ ውጭ ከላኩት ምርቶች 40 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት መቻሉን ተናግረዋል።

309 ባለሀብቶች በፓርኮቹ ገብተው ለማልማት ፍላጎት ማሳየታቸውን ተናግረው 94 የሚሆኑት የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ መግባታቸውን አስረድተዋል። በተያዘው በጀት ዓመት ፍላጎት ያሳዩት ባለሀብቶች ወደ ስራ እንደሚገቡም ተናግረዋል። በአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ገብተው እንዲያለሙ ከፍተኛ የማስተዋወቅ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው በ2016 ፓርኮቹ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ይሰራል ብለዋል።

በፓርኮቹ ገብተው ስራ የጀመሩ ባለሀብቶች ውጤታማ ስራዎችን እያከናወኑ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ለአብነትም በይርጋለም አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉት ባለሀብቶች የአቮካዶ ዘይት በማምረት በገበያ ትስስር ለ 144 አርሶ አደሮች አቮካዶ፣ ወተትና ማር እንዲያቀርቡ በማድረግ የስራ እድል መፍጠራቸውን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሀሰን ገለጻ የብድር አቅርቦት ችግር የገጠማቸውን ከባለሀብቶቹ ጋር በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ እየተደረገ ነው። ፓርኮቹን ምቹ ለማድረግም በፓርኮቹ አንድ የአገልግሎት ማዕከል መሰራቱን ተናግረው ባንክ፣ ጉምሩክ፣ የእሳት አደጋ መከላከል ብርጌድ፣ ትምህርት ቤቶች፣ የህጻናት ማቆያ እና መኖሪያ ቤቶች ተሰርተው ለሰራተኞች ስልጠና በመስጠት ሰፋፊ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን አስረድተዋል።

ለፓርኮቹ መሰረተ ልማት ግንባታ ትኩረት መሰጠቱን የሚናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው ለቡሬ ፓርክ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ 52 ሚሊዮን ዶላር በማስፈቀድና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ስምምነት በማድረግ ከማርቆስ የመስመር ዝርጋታው እየተከናወነ እንደሚገኝና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ገልጸዋል። ፓርኮቹ የውሃና የመብራት ችግሮች ተቀርፎላቸው ስራ መጀመራቸውን ተናግረው ሌሎች የጎደሉ ከስምንት እስከ ዘጠኝ ፐርሰንት የሚሆኑ ስራዎችም በአጭር ጊዜ ይጠናቀቃሉ ብለዋል።

በተያዘው በጀት ዓመትም ሁለተኛ ምዕራፍ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በተለያዩ አካባቢዎች ለመገንባት ቪዚቢሊቲ ጥናት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።



አቶ ሀሰን መሐመድ

# ‹‹ በመዲናዋ የሚገነቡ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መቀየር አለበት፣ አኗኗራችን፣ አስተሳሰባችን፣ አሠራራችን ማደግ ይጠበቅበታል፤ ታታሪ መሆን ያስፈልገናል ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ ለአፍሪካውያን የትኩረት ማዕከል፤ የእንግዳና የዓለም አቀፍ ተቋማት እንቅስቃሴዎች ማዕከል እንድትሆን፣ መቀመጫቸውን በከተማዋ ላደረጉ ዲፕሎማቶች፣ መሸመትና መዝናናት ሲፈልጉ ከአዲስ አበባ ሳይወጡ እንዲገበዩ ወይንም መዝናናት እንዲችሉ የውጭ ምንዛሬውን ማስቀረት እንዲቻል ታስቦ በፍጥነት እየተገነባ መሆኑን አመልክተዋል።

የአዲስ አበባ ዓመታዊ ገቢ በ2010 ዓ.ም. 30 ቢሊዮን፣ ወጪዋ ደግሞ ወደ 32 ቢሊዮን አካባቢ እንደነበር አስታውሰው፤ በ2015 ዓ.ም. ብቻ ወደ 109 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ ችለናል።

በ2016 ዓ.ም. 140 ቢሊዮን በጀትን እየሠራን ነው። ከዚያ ውስጥ ከ80 ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ለካፒታል ፕሮጀክት እንዲሆን፣ አስተዳደራዊ ወጪያችንንና ብክነት እየቀነስን ለዘላቂ ልማት በጀታችን እንዲውል በማድረግ እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው አንጻር በጣም ገና ነን። የንግድ እና የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱ ፍትሃዊ ከሆነ፣ ሥራን ውጤታማና ቀልጣፋ ማድረግ ከተቻለ ከዚህ በላይ ማሳካት እንችላለን ያሉት ከንቲባዋ፤ አዲስ አበባ ዋና የኢኮኖሚ ማዕከል፣ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴና ወጪ ገቢ እቃዎችም የሚንቀሳቀሱባት ከተማ እንደመሆኗ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ወደ ባለሀብትነት እንዲያድጉ መሠራቱን አመልክተዋል።

በመዲናዋ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢንዱስትሪ ፓርክ ደረጃ የማምረቻና የመሸጫ ሥፍራዎችን መገንባት መቻሉን፣ 90 ሄክታር መሬትና አንድ ቢሊዮን ብር ተመድቦ ኢኮኖሚዋን እና የማምረት አቅሟን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

አንድነት፣ ወዳጅነት፣ ወንድማማችነትና እንጦጦ ፓርኮች ትልልቅ የመስህብ ማዕከሎች ሆነዋል። ከተማዋን ከማጽዳትና ከማስዋብ ጋር አያይዘን የምንሠራው ሥራ ኢኮኖሚውን በማነቃቃት በኩል ጉልህ ሚና አለው።

ወደ ከተማዋ መጥቶ መዋዕለነዋይን የማፍሰስ ፍላጎት እየጨመረ ነው፤ የግል ግንባታዎች ብቻ ሳይሆኑ ፋብሪካዎች እና ኢንዱስትሪዎች ተነቃቅተዋል ሲሉ ከንቲባ አዳነች አብራርተዋል።

የአፍሪካ መስኮት በሚል ወደ 84 ሔክታር መሬት ላይ ቦሌ አየር ማረፊያ አካባቢ የተጀመረው ፕሮጀክት ትልቅ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን የሚያሳድግ፣ ቱሪዝምን የሚጨምር ነው። በቅርቡ የተፈራረምነውና ይፋ ያደረግነው ‹‹አዲስ ቱሞሮ›› ፕሮጀክትም ሌላው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን መሆኑን የተናገሩት ከንቲባዋ፤ አዲስ አበባን አዲስ ገጽታ ሊያላብሳት የሚችል የአዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ላይ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ፕሮጀክት እያገባደድን ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

# “ታሪክን መሰረት ባደረጉ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ቀደም ባሉ ዘመናት ያልታዩ ብዥታዎችና የአረዳድ ችግሮች አሁን ላይ ይበልጥ ተንሰራፍተዋል ያሉት የታሪክ ምሁሩ፣ ችግሮቹን በምክክር ግልጽ በማድረግ የሀገራችንን ዕድገት መሰረት እንዲይዝ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች እንዳሉን የሚካድ ጉዳይ እንዳልሆነ የገለጹት ተመራማሪው፤ እሴቶቻችን ግን የመለያያ ምክንያቶቻችን ሳይሆን የመቀራረቢያ አውዶቻችን እንዲሆኑ መግባባትን መፍጠር ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

በታሪክ ሂደቶች የተለያዩ ችግሮች አልነበሩም ማለት አይደለም፤ በደሎችም ሆነ በጎ ስራዎችን ባለፉት የታሪክ አምዶች ላይ ተከናውነዋል ያሉት የታሪክ ምሁሩ፤ አሁን ላይ ግን አዲስ ጊዜ ነው። በመሆኑም ያለፉ ቁርሾዎችንና ጉንጭ አልፋ ክርክሮችን ተሻግረን መሄድ ይገባናል ሲሉ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የሚያዋህዱንና ለዕድገታችን የሚጠቅሙን ጉዳዮች ላይ ለማተኮር ደግሞ አንዱ መንገድ ገንቢ ውይይት ማድረግ ነው ብለዋል።

ትውልዱን ዘላቂነት ባለው መልኩ ስለሀገሩ ጉዳይ ማወያየትና ስለኢትዮጵያ የተሰኙ መድረኮችን ማጠናከር የሕብረ-ብሔራዊነትን ሃሳብ ይበልጥ እንዲጎለብት ይረዳል ብለዋል።

በሀገር ጉዳይ በተለያየ መንገድ የተፈጠሩ ብዥታዎችን ለማረቅ በዘላቂነት ትውልዱን ማወያየት እንደሚገባ ጠቁመው፤ ጥርጣሬውንና አለመግባባቱን ለመቀነስ በግልጽ ጥናታዊ መሰረት የያዙ ጽሁፎችን በማቅረብ መመካከር እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስለኢትዮጵያ የተሰኘውን መድረክ በማዘጋጀት በየጊዜው ዜጎች ሃሳብ እንዲለዋወጡ የሚያደርግበት መንገድ አዋጭና ሊደገፍ የሚገባው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዕውነተኛውን ታሪክና መሬት ላይ የተሰራውን ስራ ሕዝብ እንዲያውቅ ማድረግ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር ባህሩ፤ ኢፕድ ጠቃሚ መድረኮችን እንዳዘጋጀ ሁሉ የታሪክ ምሁራንም በተደራጀና በሳይንሳዊ መንገድ መረጃዎችን ለሕዝብ ማድረስ አለባቸው ብለዋል።

በታሪኮቻችን ላይ የሰለለ መረጃ ሳይሆን ጥልቅና ሳይንሳዊ ይዘት ያላቸውን መረጃዎች በመያዝ መጻፍና መናገር እንደሚገባ የጠቆሙት ኤመሬተስ ፕሮፌሰሩ፤ በቀጣይም በታሪክ አረዳዳችን ላይ ይበልጥ ለመስራት የሚረዳ የታሪክ ምሁራን ማህበር በመቋቋሙ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል ብለው እንደሚጠብቁ ተናግረዋል።

የተለያየ አጀንዳ ያለውን ማንኛውም ሰው ተነስቶ እንደልቡ የታሪክ መረጃ የሚለቅበትና ብዥታ የሚፈጥርበት አውድ መፍጠር ሳይሆን ትውልድን ሊገነባ የሚችልና ዕውነተኛነት ላይ የተመሰረተ የታሪክ አረዳድን መፍጠር ለሀገር ግንባታ መሰረት መሆኑን ኤመሬተስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በአዲሱ ዓመት ጥንካሬዎቻችንን አጎልብተን፤ድክመቶቻችንን አርመን ለሀገራችን ብልጽግና እንትጋ!

አሮጌው 2015 ዓ.ም ጊዜውን ጨርሶ ለ2016 አዲስ ዓመት ቦታውን አስረክቧል።ሜዳ ተራራው በአበቦች አሸብርቋል፤ አደይ አበባ ወቅቷን ጠብቃ ተከስታለች፤የመስከረም ፀሐይ ምድሪቱን ማሞቅ ጀምራለች።ኢትዮጵያውያንም አዲሱን 2016 ዓ.ም በደስታና በተስፋ ተቀብለውታል።በወግና ልማዳቸው መሠረት እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህም ተባብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የራሳቸው ዘመን አቆጣጠር ካላቸው ጥቂት ሀገራት መካከል አንዷ ነች።ይህቺ ጥንታዊት ሀገር ባህሏን፤ ወጓን እና እሴቷን ጠብቃ ሺ ዘመናትን ተሻግራ ዛሬ ላይ ደርሳለች።ባህሏን ሊበርዙ፤ወግና ታሪኳን ሊያጠፉ የመጡ ባዕዳን ወራሪዎችን አሳፍራ የመለሰችና ከራሷም አልፎ ለሌሎች ጥቁር ሕዝቦች መመኪያ የሆነች ድንቅ ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያዊነት ባለብዙ ቀለማትና ባለብዙ ፈርጅ ሆኖ ትናንትን ተሻግሮ ለዛሬውም ትውልድ ኩራትና ድምቀት ሆኗል።በአዲሱ 2016 አዲስ ዓመትም ይህ አኩሪ ባህል ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።የሀገር ፍቅር፤ መስዋዕትነት፤ አገልጋይነት አንድነት እና አብሮነት የመሳሰሉት ማኀበራዊ ዕሴቶቻችን ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው።ከዚሁ በሻገርም ኢትዮጵያዊነትን የሚፈትኑና ለሀገራዊ ህልውና አደጋ የሆኑ ግጭቶችን ማስወገድና ሀገራችንን ከብልጽግና ማማ ላይ ማስቀመጥ የሁላችንም ዕቅድ ሊሆን ይገባል፡፡

አሮጌ ዓመት አልፎ አዲስ ዓመት ሲተካ ከግለሰብ ያለፈ ህልምና ዕቅድ ሊኖረን ይገባል።የግለሰብ ህልምና ዕቅድ ሊሳካ የሚችለውም የሀገር ህልም ሲሳካ ነው።ሀገር ሰላም ስትሆን ነው ያቀዱትን ማሳካት፤የወለዱትን መሳም፤የዘሩትን ማጨድ የሚቻለው።

ስለዚህም በአዲሱ ዓመት ሁሉም ለሀገሩ የሰላም ዘብ ሊሆን ይገባል። ጦርነት፤ግጭት፤ሞት፤አካል መጉደል መፈናቀል፤ ስደት በቃ ሊልም ይገባል።ልክ እንደተሸኘው 2015 ዓ.ም ጦርነት፤ ግጭት፤ አለመረጋጋት የመሳሰሉትን ጉድለቶቻችን ልናሰናብታቸው ይገባል።በምትኩም ሰላም፤ ፍቅር፤ አንድነትና አብሮነት ቦታቸውን መያዝ አለባቸው።

የሸኘነው 2015 ዓ.ም እንደሀገር በርካታ ውጤቶች ያገኘንበትና በዚያው መጠንም የተፈተንበት ዓመት ነበር።በ2015 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ጎልታ የወጣችበት፤ በግብርና ምርት አመርቂ ውጤት ያስመዘገበችበትና ሰላምንም ለማጽናት ብዙ ርቀት የተጓዘችበት ዓመት ነው፡፡

ጥቅምት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ለሁለት ዓመታት ሲካሄድ የነበረው ደም አፋሳሽ ጦርነት የቆመበትና የፕሪቶሪያው ስምምነት የተፈረመበት ታሪካዊ ቀን ነው።የፕሪቶሪያ ስምምነት ኢትዮጵያውያን ያለማንም ጣልቃ ገብነት የሀገራቸውን ሰላም ማስጠበቅ እንደሚችሉ ያሳየና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድም ግርማ ሞገስን ያላበሰ ታሪካዊ ክንውን ነው፡፡

ይህም ስምምነት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የነበረውን ጦርነት አስተማማኝ በሆነ መልኩ የቋጨና ሞት፤ የአካል መጉደል፤ ስደትንና መፈናቀልን በማስቀረት ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ልማት እንድትመልስ ያስቻለ ነው።ይህ ስምምነት ኢትዮጵያውያን የጦርነት ብቻ ሳይሆን የሰላም ጀግኖች እንደሆኑ ያሳየና በሀገሪቱ ታሪክም አዲስ ታሪክ እንዲጻፍ ያስቻለ ነው፡፡

በ2015 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን ሌላ አዲስ ታሪክ ጽፈዋል።ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 569 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል ዓለምን ጉድ አሰኝተዋል፡፡ባለፉት አራት ዓመታትም ከ31 ቢሊዮን በላይ ችግኝ በመትከልም በበረሃማነትና በአየር ጸባይ ለምትሰቃየው ዓለማችን መድህን መሆን ችለዋል፡፡

ስንዴ ከራስ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም የቀረበው በዚሁ በሸኘነው 2015 ዓ.ም ነው፡፡በዚህ ዓመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡ የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው፡፡በሩዝ ዘርፍም እየተከናወነ ያለው ተግባርም ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይነት ወደ አስመጪነት የሚያሸጋግራት ነው።

በዚህ ትውልድ ጠንሳሽነት ግንባታው በመገባደድ ላይ የደረሰው የዓባይ ግድብ በርካታ ፈተናዎችና አሜኬላዎች ቢገጥሙትም በዚህ ትውልድ አይበገሬነት ዛሬ ከራስ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት ብርሃን መሆን ችሏል።አራተኛው ዙር የውሃ ሙሌትም በመላ ኢትዮጵያውያን አንድነት በስኬት ተጠናቋል።

በ2015 ዓ.ም እንደ ሀገር ከተገኙ ስኬቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆን መቻሏ ነው።ኢትዮጵያውያን ባከናወኑት ስኬታማ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ብዙዎች የተመኙትን የብሪክስ አባልነት ኢትዮጵያውያን ማሳካት ችለዋል።ይህም ለሀገሪቱ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ይዞ የሚመጣ ነው፡፡

የ20ሺ አቅመ ደካማ ቤቶች ታድሰው በአዲሱ ዓመትም ቤት ለእንቦሳ ተብለዋል።የኮይሻ ፤የጎርጎራ፤የወንጪ፤ የሃላላ ኬላ የቱሪስት መስህቦች እየተገባደዱ ነው።በአዲስ አበባም እየተከናወኑ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች መጪው ጊዜ ብሩህ መሆኑን ያመላክታሉ።

ሆኖም ከእነዚህ ሁሉ ስኬቶች ጎን ለጎን ኢትዮጵያ በግጭትና በኑሮ ውድነት ስትፈተን ቆይታለች።እዚህም እዚያም የሚነሱት ግጭቶች ሀገሪቱ እያደረገች ያለው ግስጋሴ ላይ የራሳቸውን ጥቁር ነጥብም ጥለዋል፡፡

ስለሆነም በ2016 አዲስ ዓመት የነበሩንን ጥንካሬዎች የበለጠ የምናጎለብትበትና ድክመቶቻችንንም የምናርምበት ዓመት ሊሆን ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አዲስ ዓመት፣ ምክንያታዊ ትውልድ፣ ኃያል ሀገር!

ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ

የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ኢትዮጵያ፣ 2016 ዓ.ምን ልትቀበል ነው።ሀገሪቱና ዜጎቿ አዲሱ ዓመት ምን ይዞባ(ላ) ቸው እንደሚመጣ እርግጠኞች አይደሉም።ኢትዮጵያውያን ከአንድም ሁለት፣ ሦስት ጊዜ አዲስ ዓመት ሲመጣ መልካሙን ተመኝተውና አልመው ነበር፤በተግባር የታየው ግን ‹ይሆናል› ብለው ያላሰቡትና ያልጠበቁት ነበር።የሰላም እጦት፣ የዜጎች አሰቃቂ ሞትና መፈናቀል፣ የሀብት ዝርፊያና ውድመት … ተደጋግመው ታይተዋል።በእርግጥ ‹‹ሀገሪቱ በእነዚህ ሁሉ መከራዎች ውስጥ ሆና ስኬቶችንም አስመዝግባለች›› ተብሎ የሚነገረው ትርክትም የሚዘነጋ አይደለም።ነገር ግን ሌላው ሁሉ ይቅርና ‹‹በማንነት ምክንያት ከመገደልና ከመፈናቀል ስጋት ነፃ ሆኖ በሰላም ወጥቶ መግባትን እውን ማድረግ የተሳነውን ‹ስኬት› እንደስኬት መጥቀስ ተገቢ ነው?›› የሚለው ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ የማግኘቱ ነገር አጠራጣሪም አከራካሪም ነው።

ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ለመሆን የሚያግዟት እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፣ ግዙፍ የሰው ኃይል፣ የተከማቸ የታሪክ እርሾ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ ግብዓቶች ያሏት ሀገር ናት።እነዚህን ግብዓቶች አቀናጅታ ታላቅና ኃያል ሀገር የመሆን እድል ቢኖራትም ይህን እድል በተግባር የመተርጎሙ ነገር ግን በተጨባጭ ሊሰምር አልቻለም።ከሺ ዓመታት በፊት በበሬ የሚያርሰው የኢትዮጵያ ገበሬ ዛሬም ከዚሁ የአስተራረስ ዘዴ መላቀቅና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ ከመምራት መሻገር አልቻለም።ረሀብ ደጋግሞ ጎብኝቶን ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚለው ስም የረሀብና የችጋር ምሳሌ ተደርጎ ቆይቷል።ጦርነት የሀገሪቱ ዋነኛ መገለጫ እስኪመስል ድረስ ለቁጥር የሚታክቱ ደም አፋሳሽ ጦርነቶች በኢትዮጵያ ምድር ተካሂደዋል።የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ከውጭ ሀገራት እየተቀዱ መጥተው ሕዝብ ያለምንም ማሰላሰል እንዲሸከማቸው ተደርጎ ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል።የውሸት ትርክቶች ‹‹ለምን፣ እንዴት …?›› የሚል ጠያቂ አጥተው የአንድ ሀገር ልጆች ጎራ ለይተው እንዲጫረሱ አድርገዋል፤ በጠላትነት መፈራረጅን አስከትለዋል፤የሀገሪቱ ቅርጽ (ካርታ) እንዲቀየርም አድርገዋል።እነዚህ ችግሮች ከመቃለል ይልቅ ይበልጥ እየተወሳሰቡ መጥተው ዛሬም ኢትዮጵያንና ሕዝቧን መራራ ዋጋ እያስከፈሉ ቀጥለዋል።

አዲሱን ዓመት ስንቀበል ከምንሰናበተው አሮጌ ዓመት ጋር አብረው የማይሰናበቱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ።በአዲሱ ዓመት ሊከናወኑ የሚገባቸው ብዙ ሥራዎችም አሉ።ኢትዮጵያ ብዙ ሺ ዓመታትን ባስቆጠረው እድሜዋ ‹‹ረሀብንና ጦርነትን ደጋግማ የማስተናገዷ ምክንያት ምንድን ነው? ደጋግመው ካጋጠሟት ችግሮቿ መላቀቅ ያልቻለችውስ ለምን ይሆን?›› የሚለው ጥያቄ የሰከነ ውይይትና አጥጋቢ ምላሽ የሚፈልግ መሠረታዊ ጉዳይ ነው።ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ሌሎች አካላት ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ብዙ ምላሾችን ሰጥተዋል።ከእነዚህም መካከል የውጭ ኃይሎች ሴራ፣ መደማመጥ አለመቻል፣ የልኂቃን በጎ ያልሆኑ እሳቤዎች፣ የሕዝቦቿ ማኅበራዊ ስሪት … የሚሉት ምክንያቶች ተጠቃሽ ናቸው።ሀገሪቱ በችግሮች ውስጥ ደጋግማ የመገኘቷ ምክንያት ‹‹የመለኮታዊ ኃይል ቁጣ›› እንደሆነ የሚያምኑም አሉ።

ምክንያቶቹ የተለያዩ ቢሆኑም ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት አልተሞከረም።የአንዱን ንጉሥ ንግሥና ያልተቀበለ የግዛት አለቃ በንጉሱ ላይ ሲሸፍት፤ልኂቃን ከውጭ ሀገራት የሰሟቸውንና ያነበቧቸውን የፖለቲካና ምጣኔ ሀብት ርዕዮተ-ዓለሞች ያለምንም ማሰላሰል ወደ ኢትዮጵያ አምጥተው ሀገሪቱና ሕዝቧ ላይ ሲጭኑ ሕዝቡ ‹‹የባሰ አታምጣ›› በሚል ግራ የመጋባት ስሜት ሲቀበል፤ እሳቤዎቹን የተቃወሙ አካላት ደግሞ አለመስማማታቸውን ለመግለጽ ብረት አንስተው ‹‹ጥራኝ ጫካው›› ሲሉ … ኢትዮጵያም ባለፈችበት መንገድ ደጋግማ እየተመላለሰች ኖረች።ረሀብ፣ ጦርነትና ድህነት ደግሞ ያለማንም ከልካይ ደግመው ደጋግመው ሀገሪቱን እንዲያሰቃዩ እድል አገኙ።

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ነፃነት፣ ክብርና አንድነት ሲሉ በዓድዋና በሌሎች ስፍራዎች ለማመን የሚከብዱ ከባድና አኩሪ ተጋድሎዎችን አድርገው ነፃ ሀገር ለ‹‹ተተኪው ትውልድ›› ቢያስረክቡም ‹‹ተተኪው ትውልድ›› (በተለይ ልኂቃኑ) ግን እነዚያ መስዋዕትነቶች ያስገኟቸውን በረከቶች በመመንዘር ለታላቅ ሀገር ግንባታ ግብዓትነት ሊጠቀምባቸው አልቻለም።ታዲያ ይህን የባከነ እድል በእልህና በቁጭት የመጠቀም ኃላፊነት የወደቀው በዚህ፣ በእኛ ትውልድ ላይ ነው።ይህ ትውልድ በብሔርና በሃይማኖት ተከፋፍሎ ሀገር ለማፍረስ የሚደረገውን አሳዛኝና አሳፋሪ ግብግብ የመታገልና የመመከት አደራ አለበት።የተረሳውና የባከነው የቀደምት ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት ትርጉም እንዲኖረው እልህ አስጨራሽ ትግል ይጠብቀዋልና ለትግሉ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ መነሳት ይጠበቅበታል።

ታዲያ ቅንነት፣ ትጋትና ፅናት ተላብሶ የሀገሪቱን ችግሮች ለመፍታት በቅድሚያ የምክንያታዊ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ያስፈልጋል።ምክንያታዊ አስተሳሰብ በሌለበት ቦታ፣ ትርጉም ያለውና ተጨባጭ የሆነ ለውጥን ማሳካት አይቻልም። ኢትዮጵያ ‹‹ለምን?›› እና ‹‹እንዴት?›› ብሎ ለመጠያየቅ፣ ለመከራከርና ለመወያየት የሚያስችል የሰለጠነ ባህል አላዳበረችም።ማሰብን፣ ማሰላሰልን፣ ሚዛናዊ ዕይታንና መመርመርን የሚጠይቀው እንዲሁም ‹‹ምን?››፣ ‹‹እንዴት?››፣ ‹‹ለምን?››፣ ‹‹መቼ?››፣ ‹‹የት?›› የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ መሠረታዊና አመክንዮን የተከተሉ ወሳኝ ጥያቄዎችን በማንሳት እውነትን ከሐሰት አብጠርጥሮ የማጥራት እሳቤን የያዘው ምክንያታዊነት የተባለው ጽንሰ ሃሳብ ቦታ አላገኘም። ‹‹ማን አለ?›› እንጂ ‹‹ምን/ለምን አለ?›› ለሚለው ጉዳይ ትኩረት መስጠትን ትኩረት ነፍገነዋል።ምንም እንኳ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የቆየ አብሮ ተሳስቦና ተከባብሮ በጋራ የመኖር አኩሪ ቢኖራቸውም፣ ይህ ድንቅ መስተጋብር ግን በተለይ በፖለቲካው ዘርፍ ምክንያታዊ እሳቤን መፍጠር አልቻለም።

ሳያሰላስሉ በጅምላ የመደገፍና የመቃወም ድርጊት መለያችን የሆነ እስኪመስል እንዲሁም ‹‹ኢ-ምክንያታዊነት ብሔራዊ መገለጫችን ሆነ እንዴ?›› ተብሎ እስከሚጠየቅ ድረስ ደጋግመን ተመላልሰንበታል።ይህ የኢ-ምክንያታዊነት አስተሳሰብ ከረጅም ዓመታት በፊት ጀምሮ ዋጋ እያስከፈለን ዛሬ ላይ ደርሷል።በቂ ባልሆነ ምክንያትና ማገናዘብ የታጀበው የድጋፍና የተቃውሞ ባህላችን እንደሀገር ያገኘናቸው በርካታ የለውጥ እድሎች እንዲከሽፉ አድርጓል።ይህም ሀገራችን መድረስ የሚገባት ደረጃ ላይ እንዳትደርስ ትልቅ እንቅፋት ሆኗል፡፡

በእርግጥ ዛሬ የዓለምን ምጣኔ ሀብትና ፖለቲካ በበላይነት የሚመሩት ሀገራትም በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፈዋል።እነዚህ ሀገራት የችግሮቻቸውን ምንጮች በመገንዘብና ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት ኃያላን ለመሆን በቅተዋል።ጊዜያቸውን ለአሉባልታ መስጠትንና በትናንት ታሪካቸው ላይ ተቸክለው መቅረትን አልመረጡም፤መራራ የሆኑ እውነቶቻቸውን ያለምንም ማድበስበስ በግልጽ ተነጋግረዋል።በችግሮቻቸው ላይ በግልጽና በድፍረት ተነጋግረው መፍትሄዎችን ማስቀመጥ በመቻላቸው አሁን ለደረሱበት ታላቅነት በቅተዋል።

ታላቅ ሀገር ለመገንባትና የኃያል ሀገር ባለቤት ለመሆን የታላቅና በጎ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ያስፈልጋል።ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው መንገዶቿ በጥልቀት ተፈትሸው፤ችግሮቿና ስብራቶቿ በግልጽ ውይይት ተደርጎባቸው የእስካሁኑን የኋልዮሽ ጉዞዋን በማስቆም ወደፊት እንድትራመድ ማድረግ ይገባል።ለተደጋጋሚ ረሀብና ጦርነት የዳረጓትና ከተለመደና ከተሰለቸ የ‹‹ታላቅነት›› ወሬ ተሻግራ እውነተኛ ኃያልነትን እንዳትላበስ ያደረጓት የዘመናት ሰንኮፎቿ በግልጽ ሊነገሩና ምላሽ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል! ኢትዮጵያ ችግሮቿን በግልጽ የሚናገርላትና መፍትሄ የሚፈልግላት ልጅ/ትውልድ ትሻለች!

ምክንያታዊ አስተሳሰብን ባህሉ ያደረገ ትውልድ የመገንባት ተግባር በአንድ ጀንበር፣ በአንድ ዓመት የሚሳካ ባይሆንም ጉዞው ከአሁኑ መጀመር አለበት።ይህ ትውልድ ምክንያታዊ ትውልድ የመሆን ግዴታ ወድቆበታል።ይህን ግዴታ በብቃት አለመወጣት ግን ሀገርን የሚያሳጣ አደገኛ ዋጋ ያስከፍላል።አዲሱ ዓመት ደግሞ ስለኢትዮጵያ ችግሮች በግልጽ ተነጋግሮና ተማምኖ እውነተኛና ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የሚደረጉበት ሊሆን ይገባል! ተደጋጋሚ መከራዎች ወገቧን ያጎበጧት እናት ኢትዮጵያም ከዚህ በላይ ለመጠበቅና ጊዜ ለማባከን ዝግጁና ብቁ አይደለችም!

# ፍረዱኝ

# ከቅሬታዎች በስተጀርባ ያለው ተጨባጭ እውነት

ሙሉቀን ታደገ እና ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ስመነሻ

የዝግጅት ክፍላችን ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዚህ ገጽ €€የተቋማት አለመናበብ፤ የመረጃም ድብብቆሽ የበረታበት-የመሬት ክፍፍል‹‹ በሚል ርዕስ በአዲስ ከተማ ክፍስ ከተማ ወረዳ 14 ስለሚስተዋለው የመሬት ወረራ የደረሰንን ጥቆማ መሰረት በማድረግ ሰፋ ያለ የምርመራ ዘገባ መሥራቱ ይታወሳል። የዘገባውን ስሕትመት መብቃት ተከትሎ የተለያዩ የመንግሥት ተቋማትና ግለሰቦች ወደ ዝግጅት ክፍላችን በአካል በመምጣት እና ደብዳቤ በመፃፍ በዘገባው ላይ ያላቸውን ቅሬታ ገልጸዋል፤ እኛም በዛሬው እትማችን ለቅሬታዎቹ መልስ እንሰጣለን።

### የመረጃ ምንጮቻችን

በወቅቱ ለዝግጅት ክፍላችን ለደህንነታቸው ሲሉ ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ የአካባቢ ነዋሪዎች የመረጃ ምንጭ ሆነውናል። ምንጮቻችን በወረዳቸው የተለያዩ አካባቢዎች ‹‹አርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጆች ናቸው›› በሚል ለግለሰቦች የተመራ ቦታ አግባብነት በጎደለው መንገድ በአካባቢው ላልነበሩ ሰዎች በሙስና እየተከፋፈለ ስለመሆኑ ጥቆማ አድርሰውናል፤ እኛም ጥቆማውን መሰረት አድርገን ሙያው በሚጠይቀው መንገድ በአግባቡ የማጣራት ስራችንን ሰርተናል።

### ከወረዳ 14 አስተዳደር የቀረበ ቅሬታ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤት በቀን 26/12/2015 ዓ.ም በቀጥር ፡- አ/ከ/ክ/ወ/4/ዋ/አስ/ፅ/ቤት /2015 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ፤ በዘገባው ላይ የቀረቡ ቅሬታዎች፤ ዘገባው የተቋማትን አሰራር ታሳቢ ያደረገ አይደለም።

ለአርሶ አደር መሬት የመስጠት ሂደት፤ ወረዳ ላይ ባሉ አርሶ አደሮች ወይም በአርሶ አደር ልጆች ከሚወጣጡ የብሎክ ኮሚቴ የወረዳ አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት፤ የወረዳ መሬት ልማት ጽሕፈት ቤት በመለየት እና መረጃን በማጥራት በመመሪያ ቁጥር 20/2013 መሰረት የተለዩትን ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል። ዋና ሥራ አስፈፃሚው መረጃውንና ሂደቱን በማረጋገጥ ለክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይልካል፤ በዚህ መልኩ ይወሰናል። በጋዜጣው ላይ የወጣው ዘገባ ግን ይህንን አሰራር ታሳቢ ያደረገ አይደለም።

በልዩ ሁኔታ በፅሁፍ የቀረበው የአቶ ፍቃዱ ዳባ ይዞታ በፕላን እና በአየር ካርታ ምንም ዓይነት የመንገድ ጥናት የሌለው፤ ጥያቄ በቀረበበት ወቅት የአየር ካርታውን መሰረት በማድረግ በቀን 7/1/2013 ዓ.ም ከኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው ፤በከንቲባ ጽሕፈት ቤት በተደረገው ኦዲት ካርታው እንዲመክን እና እንዲጣራ የተደረገ ነው።


በቀን 22/09/2014 ዓ.ም በቁጥር አአኮድ/35/09/535/ አቶ ፍቃዱ ዳባ የተባሉት ግለሰብ ካርታው መምከኑ በከንቲባ ጽሕፈት ቤት ካቢኔ ተገቢ አይደለም ተብሎ በተገለጸው መሰረት መረጃው ለጋዜጠኞች ቢሰጣቸውም ይህንን መረጃ ለመጠቀም ፈቃደኝ አልሆኑም።

በጋዜጣ ላይ የወጣው የአቶ ፍቃዱ ዳባ ካርታ ወይም የባለይዞታ የምስክር ወረቀት በካርታ ቁጥር 14/02/1/1703/32187/00 የተሰጠበት ቀን 7/1/2013 ዓ.ም የሚል ሲሆን፤ ሆን ተብሎ ካርታው አሁን አዲስ እንደተሰራ በማስመሰል የፊት ገጽ ላይ መቅረቡ ተገቢነት የሌለው ፤ መታረም አለበት የሚል እና ሌሎች ሀተታዎችን የያዘ ነው። የቅሬታውን ሙሉ ጽሁፍ በአባሪ መልክ አቅርበነዋል።

### የዝግጅት ክፍሉ ምላሽ

የዝግጅት ክፍሉ ከነዋሪዎች የደረሰውን ጥቆማ ይዞ በጉዳዩ ዙሪያ ከወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረጉ ይታወሳል። የደረሰን ጥቆማ በወረዳው የተለያዩ ቦታዎች መሬት ያለአግባብ ለማይመለከታቸው አካላት እየተላለፈ ነው የሚል ስለነበር በቃለ መጠይቁ ወቅት የተወሰኑ ግለሰቦች መረጃ በተለየ ሁኔታ አልተጠየቀም። የዝግጅት ክፍላችን ያቀረበው ጥያቄ፤ አቶ ፍቃዱ ዳባ ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን

**ቅሬታዎችን ማቅረብ በዝግጅት ክፍላችን አግባብነት ያለው መሆኑ ቢታመንበትም የዝግጅት ክፍሉ ከመልካም አስተዳደር ጋር ለሚነሱ ጥያቄዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች በወቅቱ መረጃዎችን በመስጠት የሥራው ተባባሪ መሆን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት ከሚንቀሳቀስ ተቋምና የተቋም አመራር የሚጠበቅ ነው፤ ከዚህ አንፃር ቅሬታ አቅራቢ ተቋማት የመረጃ አሰጣጥ ሥርዓታቸውን መልሰው ቢያጤኑት መልካም ነው**


A/ K/ S/C/ ADMIN/FARMERS AND URBAN AGRICUL TRADE DEVELOPMENT OFFICE

አከከከ/የአ/አ/ከ/ግ/ል/ጽ/ቤት 132 /2015
Ref.No.
Date
ቀን 29 12/2015

ለአቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ

አዲስ አበባ


ጉዳዩ፡- አርሶ አደር መሆንን ማሳወቅን ይመለከታል

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አርሶ አደር አቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ በቀን 26/12/2015 ዓ/ም በፃፉት ማመልከቻ አርሶ አደር መሆነን እና በአርሶ አደር እና በአርሶ አደር ልጆች መመሪያ መሰረት መስተናገደን የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት መረጃ ይሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል።

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት በወረዳ 14 አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጆችን በመመሪያው ቁጥር 20/2013 መሰረት የተለዩ አርሶ አደር መሆናቸው በደብዳቤ ቁጥር አ/ከ/ክ/ከ/ወ/14/አ/አ/አ/ከ/ግ/ል/ጽ/ቤት/335/2014፣ በቀን 15/11/2014 ዓ/ም ከወረዳ የ2013 አርሶ አደር መረጃ ፀድቆ የተገለፀልን ሲሆን አሁንም በደብዳቤ ቁጥር አከ/ክ/ከ/ወ/14/አ/አ/አ/ከ/ግ/ል/ጽ/ቤት/024/2015፣ በቀን 25/12/2015 ዓ/ም በድጋሚ አርሶ አደር መሆናቸው ያሳወቁን ሲሆን አቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ በመመሪያው መሰረት ከተለዩት እና መብት ከተፈጠረላቸው ዝርዝር ውስጥ መኖራቸውን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

ብርሃኑ ነገራ ዋቅጅራ
Birhanu Negera Wakjira
የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ፅ/ቤት ኃላፊ
Farmers and Urban Agriculture
Development office Head




ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# ከቅሬታዎች በስተጀርባ...

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 አስተዳደር ዋና ስራ አሰፈፃሚ ጽ/ቤት

Addis Sub City Ketema Woreda 14 Administration Executive Head Office

ቁጥር :- አ/ከ/ክ/ወ/14/ዋ/አስ/ፅ/ቤት /2015 ዓ.ም
ቀን 26/12/2015 .ዓ.ም

ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ

ጉዳዩ :- የተቋማት አለመናበብ እና የመረጃ ድብብቆሽ የበረታበት የመሬት ከፍፍል ተብሎ ነሐሴ 24/2015 ዓ.ም

በወጣው ፅሁፍ ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

በዋናነት ጥያቄ የቀረበባቸው ወይም ፕላን ተቃርኖ ናቸው ተብሎ የተጠየቁት 11 ይዞታዎች ሲሆኑ መብት የተፈጠረለት ግለሰብ ይገባሀል ተብሎ ከተረጋገጠለት በዋላ ያለ ግለሰቡ ፍቃድ በጋዜጣ የፊት ገፅ ላይ መውጣቱ ተገቢ ያልሆነ እና ሰብአዊ መብትን የሚጥስ በመሆኑ መታረም አለበት ::
ፕላን ፎርማት እና የአየር ካርታ አያይዘናል ቦታዎች አሁንም በአየር ካርታ እንዲሁም ፕላን ተቃርኖ የሌላቸው መሆኑን ይህን የሚያረጋግጥልን ይሆናል :: ነገር ግን የአርሶ አደር ስራ እንደሚታወቀው ወረዳ ላይ ባሉ አርሶ አደሮች ወይም በአርሶ አደር ልጆች ከሚወጣጡ የብሎክ ኮሚቴ የወረዳ አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ፅ/ቤት ፤ የወረዳ መሬት ልማት ፅ/ቤት በመለየት እና መረጃን በማጥራት በመመሪያ ቁጥር 20/2013 መሰረት የተለዩትን ለወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ ያቀርባል ዋና ስራ አስፈፃሚው መረጃውንና ሂደቱን በማረጋገጥ ለክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ፅ/ቤት ይልካል ነገር ግን በፅሁፍ ጋዜጣ ላይ የቀረበው በመመሪያ የተቀመጠውን እንዲሁም ግለሰባዊ በሚያስመስል ሁኔታ የሚፃረር ፅሁፍ እንዲታረም ::
በልዩ ሁኔታ በፅሁፍ የቀረበው የአቶ ፍቃዱ ዳባ ይዞታ በፕላን እና በአየር ካርታ ምንም ዓይነት የመንገድ ጥናት የሌለው ጥያቄ በቀረበበት ወቅት የአየር ካርታውን መሰረት በማድረግ በቀን 7/11/2013 ዓ.ም ከኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ካርታ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸው ሲሆን ነገር ግን በከንቲባ ጽ/ቤት በተደረገው ኦዲት ካርታው እንዲመክን እና እንዲጣራ የተደርገ ሲሆን በቀን 22/09/2014 ዓ.ም በቁጥር አአኮድ/135/09/535/ የአቶ ፍቃዱ ዳባ የተባሉት ግለሰብ ካርታው መምከኑ በከንቲባ ፅ/ቤት ካቢኔ ተገቢ አይደለም ተብሎ በተገለፅው መሰረት መረጃው ለጋዜጣኞች ቢሰጣቸውም ይህን ወደ ጎን በመተው ህዝብ እና መንግስትን እንዲሁም በተቋማት መካከል መረጃ ድብብቆሽ እንዲሁም በመመሪያ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ውሳኔ የተላለፈውን ይዞታን የመሬት ክፍፍል እና ቅርምት አድርጎ በማስመሰል ማቅረብ ተገቢነት የሌለው መሆኑ ታውቆ በድጋሚ መረጃ ታይቶ እንዲስተካከል እንላለን :: ይህ ጉዳይ አርሶ አደሩ የዘመናት ጥያቄ ከብዙ በደል በዋላ ይገባሃል ተብሎ መብት የተፈጠረለትን ባለጉዳይ ያልተገባ እንግልት የሚዳርግ እና መረጃ እያለ እንደሌለ አድርጎ ማቅረብ ከስነ-ምግባር እና የጋዜጠኛነትን ሙያ አለመሆኑ በመረዳት ማስተካከያ እንዲደረግ :: ሆኖም አሁን በጋዜጣ ላይ የወጣው የአቶ ፍቃዱ ዳባ ካርታ ወይም የባለይዞታ የምስክር ወረቀት በካርታ ቁጥር 14/02/1/1703/32187/00 የተሰጠበት ቀን 7/11/2013 ዓ. ም የሚል ሲሆን ሆን ተብሎ ካርታው አሁን አዲስ እንደተሰራ በማስመሰል የፊት ገጽ ላይ መቅረቡ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ መታረም አለበት :: በፅሁፍ ላይ የቀረቡት የህይወት ምንጭ እየሱስ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ከአርሶ አደር ይዞታ ጋር በፍፁም የማይገናኝ በመሆኑና ግንቦት/23/2014 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አአከፅ/17/3040/5 በአዲስ አበባ ከንቲባ ፅ/ቤት የካቢኔ ውሳኔ መሰረት የተላለፈ እንደ ሆነ ይጣወቃል :: ወረዳ አስተዳደር በከንቲባ ጽ/ቤት የተወሰነውን ውሳኔ የፈፅምን መሆኑንና ነገር ግን ቦታው ቀደም አምልኮ ይፈፅበት የነበረው ይዞታውን ለምን

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 አስተዳደር ዋና ስራ አሰፈፃሚ ጽ/ቤት

Addis Sub City Ketema Woreda 14 Administration Executive Head Office

አይለቁም ለተባለው የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/መ/የማ/ን/መ/223/21053/01 ካርታው የተሰጠበት ቀን 25/04/2008 ዓም በግዥ ያገኙት በወ/ሮ ዘነበች ገሰሰ ባይለየኝ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን የግል ንብረታቸው እንጂ የቤተክርስቲያኑ ንብረት ስላልሆነ ማስለቀቅ አንችልም በመሆኑም ለቤተክርስቲያን በእምነት ቦታነት ያልተሰጠ መሆኑ ታሳቢ ሳይደረግ በሁለት እምነት ተከታይዎች መካከል ግጭት ቀስቃሽ ፅሁፍ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ነሐሴ 24 2015 ዓ.ም እትም ማውጣቱ ተገቢነት የሌለውና ሌላ የፓለቲካ አጀንዳ ካልሆነ በስተቀር የእስልምናም ሆነ የፕሮቴስታንት አማኞች በማይጠቅም ሁኔታ በህትም ማቅረቡ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ መታረም አለበት :: በተጨማሪም ወረዳ የመጡት ጋዜጠኞች የጠየቁት ጥያቄ ሚሽን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ለአርሶ አደር መብት የተፈጠረለት 150 ካሬ ላይ የሚገኘውን ቤት ለአምልኮነት ተከራይተው የሚገለገሉበት ነው ብለን ማብራሪያ የሰጠን ሲሆን ነገር ግን ጋዜጠኞቹ ለአዲስ ከተማ ክ.ከተማ መሬት አስተዳደር ያቀረቡት ጥያቄ ከህይወት ምንጭ እየሱስ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ጋር በማገናኘት በኪራይ ተከራይተው አምልኮ ስለሚያካሂዱ ሌላ ቤተ እምነት ነው:: ቤተ እምነቱም ስሙ የክርስቶስ ሽታ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ይባላል ሁኔታው፣ ከህይወት ምንጭ እየሱስ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ባለመረዳት ይሁን ሆን ተብሎ በጉዳዩ ከህይወት ምንጭ እየሱስ ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለአርሶ አደር ልጅ ከተላለፉት ይዞታዎች መሐከል አስመስሎ ማቅረብ ተገቢ አይደለም መስተካከል አለበት :: ሁለት የማይገናኙ ጉዳይዎችን በማገናኘት ተገቢ አለመሆኑን እየገለጽን ሆን ተብሎ በወረዳ እና በክፍለ ከተማ አስተዳደር መካከል አለመናበብ አለ ብሎ ሳያረጋግጡ እትም ላይ ማውጣት ተገቢ ስላልሆነ መታረም አለበት :: አርሶ አደሮች በአሰራር እና በመመሪያ መሰረት ያገኙትን መብት ወደ ጎን በመተው በሚያሸማቅቅ መልኩ የመሬት ከፍፍል ተደርጓል በሚል ተጨባጭነት በሌለው ጥቆማ እና መረጃን መሰረት ያላደረገ የጥቆማ እና የማጣራት ውጤት አስመስሎ ማቅረብ ስህተት ስለሆነ የጋዜጠኝነትን ስነምግባር ወደ ጎን በመተው እውነትን መሰረት ያላደረገ በችኮላ ሚዲያ ላይ ማውጣት የተቋሙን ታአማኝነት የሚያሳጣና እና ጥርጣሬ ውስጥ የሚከት ስለሆነ ትክክለኛውን መረጃ በድጋሚ አርሞ እንዲያቀርቡ እና የእርምት ማስተካከያ እንዲደረግበት እያሳሰብን ይህ ካልሆነ በስም ማጥፋት በህግ የምንጠይቅ መሆኑን እንገልጻለን ::

ግልባጭ
ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ግብርና እና አርሶ አደር ኮሚሽን
ለአዲስ ከተማ ከፍለከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ
ለአዲስ ከተማ ከፍለከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ፅ/ቤት
ለአዲስ ከተማ ከፍለከተማ አርሶ አደር ከተማ ግብርና ጽ/ቤት
ለአዲስ ከተማ ከፍለ ከተማ ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ከሰላምታ ጋር

Addis Ababa city Government Addis Ketema Woreda 14 Administration office

Guluma Tola

ከገጽ 6 የዞረ

ከ10 ያላነሱ ግለሰቦችን ፋይል የማጣራት ነው።

በወቅቱ የዝግጅት ክፍላችን ያቀረባቸው ጥያቄዎች፤ ቦታውን የወሰዱት እና ቦታው ይገባቸዋል በሚል ውሳኔ የተላለፈላቸው አርሶ አደሮች ናቸው? የወረዳው ነዋሪ ናቸው? ሥራ አስፈጻሚውም የሰጠን ምላሽ «አዎ የዚህ ወረዳ ነዋሪዎች ናቸው» የሚል ነበር። ይህን ተከትሎ የአርሶ አደር ልጅ ስለመሆናቸው እና የቀጠና ኮሚቴዎችም አርሶ አደር እና የዚህ ወረዳ ነዋሪ ስለመሆናቸው ከወረዳ 14 ሲቪል ምገባና ነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ፋይላቸው ይጣራ? የሚል ጥያቄ ለአቶ ድሪባ አቅርበን ነበር።

ይሁንና አቶ ድሪባ የሲቪል ምገባና ነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ፋይል ለማየት ከፈለጋችሁ መስሪያ ቤታችሁ በሌላ ደብዳቤ ይጠይቀን የሚል ምላሽ ሰጥተውናል። የዝግጅት ክፍሉ ጋዜጠኞችም አሁን መረጃ እየሰጡን ያለው ህጋዊ ደብዳቤ ስላመጣን ነው። በደብዳቤው መሰረት ሁሉን አቀፍ መረጃ ቢሰጡን ምን የአሰራር ችግር ይፈጥራል የሚል ተጨማሪ ጥያቄ አቅርበዋል።

ሥራ አስፈጻሚው ሌላ ደብዳቤ ጽፋችሁ ካልመጣችሁ መረጃውን አልሰጥም በማለታቸው ሌላ ደብዳቤ በማዘጋጀት ወደ ቦታው ተመልሰናል። ይህም ሆኖ ግን ደብዳቤውን ይዘን በቀጠሮ ቀን ስንሄድ አቶ ድሪባ አልነበሩም። የወረዳ 14 ሲቪል ምገባና ነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ኃላፊም አልተገኙም። ይልቁንም ነዋሪዎች ብቻ ተሰብስበው ነበር።

ወረዳ 14 ሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ባለሙያዎች እነዚህ ነዋሪዎች ናቸው ወይስ አይደሉም? መረጃ ስጡን ብለን ጠይቀናል። ባለሙያዎቹም በግለሰቦቹ የመሬት ካርታቸው መሰረት ጥያቄያችንን ተቀብሎ መረጃ ለመስጠት ያደረጉት ጥረት አልተሳካም። ከሰዓታት ቆይታ በኋላ በመታወቂያቸው ካልሆነ በቀር በመሬት ካርታቸው መሰረት ነዋሪ መሆናቸውን የሚያሳይ ሰነድ እንዳላገኙ አሳውቀውናል። በመሆኑም የዝግጅት ክፍላችን በወቅቱ ተገቢውን መረጃ አለማግኘቱን ለማሳወቅ ተገዷል። የአቶ ፍቃዱ ዳባ ካርታ ወይም የባለይዞታ የምስክር ወረቀት በተመለከተም በእጃችን ያለውና ለህትመት የበቃው መረጃ ከወረዳው ያገኘነው ነው።

### የአቶ ፍቃዱ ዳባ ቅሬታ

አቶ ፍቃዱ ዳባ ለዝግጅት ክፍላችን ባቀረቡት ቅሬታ፤ አቅም ደካማ በመሆናቸው በሌሎች ድጋፍ እንደሚኖሩ ነግረውናል። በዚህ የመሬት ጉዳይ መፍትሄ ፍለጋ በየተቋማቱ ብዙ ውጣ ውረዶችን ማሳለፋቸውን ጠቁመውናል። ለዘመናት ለግብርና ሥራ ሲጠቀሙበት የኖረውን መሬት ያለአግባብ በመወሰዱ በተደጋጋሚ ለካሳ ክፍያ እና መብታችን ለማስከበር ለፍትህ ሲጮሁ እንደነበር፤ አሁን ያገኙት አንገት ማስገቢያ ቢያንስ እንጂ የሚበዛባቸው እንዳልሆነ ገልጸውልናል።

ሌላው ቀርቶ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በመሬታችን ላይ ተገንብተው ሲከፋፈሉ እኛ «የበይ ተመልካች» ሆነን ኖረናል። ይሁንና ለዘመናት ዋጋ የከፈልንበት ጉዳይ በእኛ ጥረትና በመንግሥት ይሁንታ ፍትህ ማግኘቱ የማይዋጥላቸው ግለሰቦች ዱካችንን እየተከተሉ የተሳሳተ መረጃ እየሰጡ እንደሆነ ጠቁመውናል። ለዝግጅት ክፍላችን፤ የወረዳ ነዋሪ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ መታወቂያ እና የሚመለከተው የመንግሥት አካል የሰጠኝ ነው ያሉትን ካርታ አቅርበዋል።

### ሲቪል ምዝገባና ነዋሪነት አገልግሎት ጽሕፈት ቤት ቅሬታ

ያለ አግባብ በጋዜጣ የወጣ ስም ማጥፋት እንዲስተካከል መጠየቅን ይመለከታል በሚል ርዕስ፤ ጽሕፈት ቤቱ ነሐሴ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ለዝግጅት ክፍሉ በላከው ደብዳቤ፤ በአቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ ጉዳይ በጽሁፍም በቃልም መረጃም ይሁን ማስረጃ የተጠየቅነው ነገር የለም፤ ባልተጠየቅንበት አግባብ መረጃ አልሰጡም ተብሎ ነሐሴ 24 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ስማችን መጠቀሱ ተገቢ አይደለም ብሏል።

በምላሹም፤ አቶ ፍቃዱ ዳባ በዳዳ በቤት ቁጥር 887/ሀ እና በቤተሰብ ቅጽ 01 ላይ ተመዝግበው የሚገኙ የወረዳቸው ነዋሪ መሆናቸውን፣ ከዚህም በላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 443/1993 ዓ.ም ውሳኔ ያገኘ የኑዛዜ መረጃ በጽሕፈት ቤቱ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

### የዝግጅት ክፍሉ ምላሽ

የዝግጅት ክፍላችን መረጃዎች ለማጥራት በተደጋጋሚ በወረዳው ተመላልሷል፤ ለህትመት የበቁ ዶክመንቶችን ጭምር ከወረዳው መውሰዱም ይታወቃል። በተጨማሪም የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚው አቶ ድሪባ በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ቢጠየቁ፣ ሌላ ደብዳቤ ካልተፃፈ መረጃ አልሰጥም በማለታቸው ተቋማችን ሌላ ደብዳቤ ለመፃፍ የተገደደበት ሁኔታ እንደነበር ቀደም ብለን ለመግለጽ ሞክረናል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው በጠየቁት መሰረት ተጨማሪ ደብዳቤ ጽፈን መረጃ ለማግኘት ያደረግነው ጥረት በሳቸው ፈቃደኝነት ማጣት ሳይሳካ ቀርቷል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን ለህትመት በበቃው ዘገባ ላይ ያሉ አንዳንድ መረጃዎች ከተቋሙ ባለሙያዎች የተወሰዱ መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም ፣ ከዚህ የተነሳም በጉዳዩ ዙሪያ መረጃ አልተጠየቅንም በሚለው የቀረበው ቅሬታ አግባብነት የጎደለው ነው።

### ከኤሌክትሪክ አገልግሎት የተገኘ ተጨማሪ መረጃ

ምንም እንኳን የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ምንም የፕላን ተቃርኖ የለውም ቢሉም፤ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪክት ቁጥር 1 ሥራ አስኪያጁ ከፍተኛ ኃይል ቀርቶ አነስተኛ ኃይል ቢሆንም በግለሰቦች ጣሪያ ላይ ማለፍ እንደሌለበት ገልጸዋል።

በወቅቱ የዝግጅት ክፍላችን ምሰሶው በሚያልፍባቸው ቦታዎች ላይ ሕንፃዎችን መገንባት ይቻላል ወይ? ቤት የሚገነቡ ካሉስ ተቋማችሁ መብቱን እንዴት ያስጠብቃል? ተብለው የተጠየቁት የምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪክት ቁጥር 1 ሥራ አስኪያጁ አቶ ወንድወሰን ፈዬራ እንደገለጹት፤ መሬት የሚሰጠው ሌላ አካል ነው። የመብራት ኃይል የሚሰራው የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ብቻ ነው።

መስመር ከተዘረጋ በኋላ ቤቶች ቢገነቡ የቤት ግንባታ ጋር የሚያገናኘው አካል ነው መጠየቅ ያለበት እንጂ የእኛ ተቋም አይደለም። ሆኖም መስሪያ ቤቱ በሰዎች መኖሪያ ቤት ላይ ከባድ ኃይል ተሸካሚ ገመድ መዘርጋት ይቅርና በአጥር ላይ እንኳን ዝቅተኛ ኃይል ተሸካሚ ገመድ አይዘረጋም ብለዋል።

የኃይል ተሸካሚ መስመር ተዘርግቶ ከነበር እና በኃይል ተሸካሚው ገመድ ስር ግንባታ ማከናወን የሚፈልግ ሰው በመመሪያው መሰረት ማዘዋወሪያ ይጠይቃል። ለማዘዋወሪያው ክፍያ ይከፍላል። በመቀጠልም የኃይል ተሸካሚ መስመር ማዘዋወር ግዴታቸው መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህ አግባብ ለሚመጡ ሰዎች የማዘዋወር ሥራ እየሠራን ነው ነው የሚሉት ሥራ አስኪያጁ፤ አሁን ውዝግብ በተነሳበት ቦታ ግን ማንም አካል ጥያቄ ለተቋማቸው እንዳላቀረበና ስለጉዳዩም ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዝግጅት የምርመራና መልካም አስተዳደር ክፍል መስማታቸውን አስረድተዋል።

### በመሠረታዊነት ሲታረሙ የሚገባቸው ጉዳዮች

ከሁሉም ቀድሞ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የወረዳ 14 አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ለዝግጅት ክፍላችን የመጣው ደብዳቤ ቁጥር በአግባቡ አለመፃፉ፤ በቅሬታውም በተደጋጋሚ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የፊት ገፅ በወጣ ዘገባ የሚል ትችት አለበት። እውነታው ወረዳውን በተመለከተ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የፊት ገጽ የወጣ ዘገባ የለም። ይልቁንም በገጽ 6 እና 7 ፍረዱኝ በሚል ዓምድ የተስተናገደ ነው።

ሌላው ዝግጅት ክፍሉ ለክፍለ ከተማው ሆነ ለሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት ስለአቶ ፍቃዱ ዳባ ጉዳይ በተለየ ሁኔታ መረጃ አልጠየቀም። የአቶ ፍቃዱ ዳባን ጉዳይም በተለየ ሁኔታ የማየት ፍላጎት የለውም። የዘገባው ዓላማ አጠቃላይ በሆነው የነዋሪዎች ቅሬታ ዙሪያ ነው።

ዘገባው የመልካም አስተዳደር /የመሬት ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ ለጉዳዩ ሃይማኖታዊ ይዘት ሰጥቶ ፤የተሰጠውያልተገባ አስተያየት ከአንድ ኃላፊነት ከሚሰማው ተቋም የሚጠበቅ አይደለም። የዝግጅት ክፍሉ ለሃይማኖቶች መቻቻልና መከባበር አበክሮ የሚሠራ ስለመሆን የማንንም ምስክርነት የማይፈልግ፤ የዕለት ተዕለት ሥራዎቹ ተጨባጭ ማሳያ ሆነው የሚገልጹት ነው።

ቅሬታዎችን ማቅረብ በዝግጅት ክፍላችን አግባብነት ያለው መሆኑ ቢታመንበትም የዝግጅት ክፍሉ ከመልካም አስተዳደር ጋር ለሚነሱ ጥያቄዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለማግኘት ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች በወቅቱ መረጃዎችን በመስጠት የሥራው ተባባሪ መሆን ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት ከሚንቀሳቀስ ተቋምና የተቋም አመራር የሚጠበቅ ነው፤ ከዚህ አንፃር ቅሬታ አቅራቢ ተቋማት የመረጃ አሰጣጥ ሥርዓታቸውን መልሰው ቢያጤኑት መልካም ነው።

## ነፃ ሃሳብ

# ብሔራዊ ምክክር - ዘላቂ ሰላም

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለተሻለ ሀገራዊ ተግባቦት በብሔራዊ ምክክር በኩል እንቅስቃሴ እያደረገች እንደሆነ ይታወቃል። ይሄም እንቅስቃሴ በተመረጡ ባለሙያዎች ለዓመታት ቅድመ ዝግጅት ተደርጎበት ወደ ሥራ ሊገባ ቀናቶች እየቀሩት ነው።

እንደ ሀገር የተደቀኑብንን ማናቸውንም አይነት ፈተናዎች በጦርነት ሳይሆን በሰላም፣ በጥላቻ ሳይሆን በይቅርታ ለመሻገር እየተደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው። እንዲህ አይነቱ ዘመነኛ እሳቤ ከትናንት ወደዛሬ መጥተው እድፍ ያለበሱንን የፖለቲካ ትኩሳቶች ሽሮ አንድነትን እንደሚሰጠን ይታመናል።

አንድ እግራችን ትናንት ላይ አንዱ ደግሞ ዛሬ ላይ ቆሞ በመንታ ልብ ጥንድ ሃሳቦችን ስንካድም ከሚገባን ፊተኝነት ተቆራርጠናል። ወዴት እንደምንሄድ መንገድ ጠፍቶን አሻጋሪ ስንፈልግ ታይተናል። አዲስ መንገድ መስራት አቅቶን በተራመድነው መንገድ ላይ ተጋግመን ስንመላለስ ዓመታት ተቆጥረዋል።

እነዛ ከመሄድ ባለፈ፣ ከድካም ባለፈ ብርታት ያልሰጡን ጎዳናዎች ዛሬ ላይ በምክክርና በውይይት ሎጥ የሄደባቸው የጺጋ ጎዳናዎች እንዲሆኑ ተረት ወለድ ትርክቶቻችንን ሽረን በእርቅና በመተቃቀፍ ዳግም ልንሄድባቸው ጥርጊያ ጀምረናል። ለአዲስ ሃሳቦች ቅድሚያ ሰጥተን ያለፈው የቁርሾ ጊዜ ባለፈ አስተሳሰብ ስር እንደነበር አምነን በመቀበል አዲሱን የእርቅ መንገድ በአዲስ ሃሳብ ለመጀመር እያሟሟቅን ነው።

ብዙ ተራምደን ወደረፍት የሚወስድ የማርያም መንገድ ያላገኘነው ልባችንን ከጥላቻ ስላላጸዳን ነው። ማናችሁ ስንባል ኢትዮጵያዊ ነን እንላለን በማንነታችን ውስጥ ግን ከአባቶቻችን የወረስነው የአንድነትና የፍቅር እውነት የለም። ይሄን መሰሉ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በመለያየት ውስጥ መቆም የደስታ መንገዳችንን ሰውሮብናል።

ኢትዮጵያዊ ሆኖ እኔነት የለም። ኢትዮጵያዊ ሆኖ ዘረኝነት የለም። ኢትዮጵያዊነት መነሻው አንድነት መድረሻውም እኛነት ነው። የአባቶቻችን ሀገር የመፍጠር ዓላማ ከዛም ባለፈ ሀገር የማጽናት እውነት በዚህ አንድነትን መሰረት ባደረገ የመነሻና የመድረሻ እሳቤ ውስጥ የጸና ነው።

እኛ የዛኛው ትውልድ በአንድነቱ ሀገር የሠራው የአባቶቻችን መልክ ነን። በዚህ መልክ ውስጥ የብሄር ሽኩቻ፣ የእኔነት ውዳሴ የለም። ይሄ መልክ በኢትዮጵያዊነት የቆነጀ፣ በህብረ ብሄራዊነት ያጌጠ የብዙሃነት ቀለም ነው። ከብዙሃነት ውስጥ እኔ ብለን ራሳችንን ብቻ ስናወድስ ኢትዮጵያዊነት የተሠራበትን የጋራ እውነት እያላላን ነው።

ዛሬ ላይ ጠብቆ ተገምዶ ግን ደግሞ የላላው የአባቶቻችን እውነት ከብዙ ማንነት ውስጥ ራሳችንን ብቻ የማድመቃችን፣ የማወደሳችን፣ የመነጠላችን፣ የማሞካሸታችን ጣጣ ነው። በብሄር ስም ተቧድነን፣ ከትናንት አብራክ ውስጥ ነውር እየመዘዝን የምንጠላላው ጥላቻ፣ የምንቀያየመው ቅያሚ የጸነሰው ጋፍ ጽንስ ነው።

የድህነት አቀበት በመያያዝ የሚታለፍ ነው። ሳይያያዝና በአብሮነት ሳይቆም ታሪኩን የለወጠ ሀገርና ሕዝብ የለም። የስልጥኖቹን የስልጣኔ ታሪክ ብናጠና የሀገር ፍቅር ስሜታቸው ከእኛነት መንፈስ ውስጥ እንደፈለቀ እንደርስበታለን። በተቃራኒው ብዙ ሕዝብ ይዘው፣ ብዙ የተማረ የሰው ኃይል አቅፈው፣ በወጣትና በተፈጥሮ ደምቀው ግን ደግሞ ከምኞት ባለፈ ከነበሩበት ፈቀቅ ያላሉ ሀገራት ጥቂቶች አይደሉም። የእኚህን ሁለት ሀገራት የአስተሳሰብ አድማስ ብንፈትሽ እኔነትና እኛነት ሆኖ እናገኘዋለን።

እኛ ብለን እስካልተነሳን ድረስ ልዩነትን መፍጠር አይቻለንም። እኔነት ብዙዎች ለብቻቸው ኖረው፣ ለብቻቸው አስበው፣ ለብቻቸው የሚሞቱበት መቃብር ነው። ታላቁ ሩሲያዊ ደራሲ ፊዮዶር ዶስቶፍስኪ ይሄን የእኔነት እሳቤ ተንተርሶ እንዲህ ብሎ ነበር ‹እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ሲኦል ማለት ሌሎችን አለማፍቀር የሚፈጥረው የሕመም ስሜት ነው› ፤ ራስን ከሌሎች መነጠልን ክፉ ከሆነችው ሲኦል ጋር አዛምዶታል።

አንድ አይነት ሆነን ከትናንት ወደዛሬ የመጣነው አንድ አይነት ሆነን ስለቆም ነው። እድሳት ያስፈልገናል። ዘመኑ ከትናንት ዛሬ ሌላ ነው። ዓለም በስልጣኔው ሩቅ በደረሰበት በዚህ ስልጡን ዘመን ላይ በትናንት ፖለቲካ፣ በትናንት ጥፋት፣ በትናንት ትርክት ዛሬን መኖር ከምንም የማይወዳደር ጥፋት ነው።

እኔነት ከነውርና ስር ከሰደደ ራስ ወዳድነት ባለፈ ለትውልዱ መጥፎ የሚያስተምር፣ በራስና በሀገር ላይ መጨከን ነው። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በራሳችን ላይ ጨክነናል። በምናስበው ሃሳብ፣ በምናራምደው እምነት እየጎዳን ያለነው ራሳችንን ነው። የሚጠቅመን በጋራ ሃሳብ የጋራ ጥቅማችንን መፍጠር ነው።

ሃሳቦቻችን ወደጥፋት ከማምራታቸው በፊት የሚገራ፣ የሚያቀና እውቀት ያስፈልገናል። ያልገባን እንዲገባን የገቡን የስህተት እውነቶች መሻር አለባቸው። አሁን የሚያስፈልገን ያልገባን እንዲገባን ነው። ከገቡን ይልቅ ያልገቡን እንደሚበጁን ገብቶናል ባለው ፖለቲካና ፖለቲከኞች የደረሰውን ጥፋትና ውድመት ማየቱ በቂ ነው።

ረፍታችን ያለው ባልገቡን እውነቶች ውስጥ ነው። ያልገቡን እውነቶች እንዲገቡን ራሳችንን በኢትዮጵያዊነት ስነምግባር ማነጽና የአባቶቻችንን ሀገር የመፍጠር እውነት መከተል አለብን። ያልገቡን እንዲገቡን ሰላምን በጦርነት ከማምጣት እሳቤ ወጥተን ከጦርነት በፊት ሰላም፣ ከጥላቻ በፊት ፍቅርን የሚል አዲስ እውቀት ሊዋሃደን ይገባል።

በኢትዮጵያ ስዕል ውስጥ የሁላችንም ብሩሽ አለ። ኢትዮጵያን የሳላት የሁላችን ሃሳብ፣ የሁላችን ሥርዓት ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ቢጎል ደብዛዛዋን ኢትዮጵያ ነው የምናገኘው። የብኩርና ግፊያችን ማናችንንም ፊተኛ አያደርግም። ኢትዮጵያን ከመጣል፣ አንድነታችንን ከመነቅነቅ ባለፈ የሚጨምርልን የኃይል አቅም የለም።

ወዳልገቡን እውነቶች እንማትር። ፖለቲካው ያስተማረንን፣ ፖለቲከኞቻችን የሰጡንን የእኔነት ሃሳብ ሽረን የአባቶቻችንን እውነት እንከተል። ለእውነትና ለእርቅ ከተጠቀምነው ብሄራዊ ምክክር መንገድ የሚሰጠን ነው። በጥላቻ የዘጋነውን፣ በራስ ወዳድነት የራቅነውን የእረፍት መንገድ የሚቀድልን ነው።

መንገድ ያስፈልገናል። ወደሰላም መሄጃ፣ ወደአንድነት ማስተዋያ መንገድ። መንገድ ያስፈልገናል ወደእርቅ፣ ወደፍቅር የሚወስድ።መንገዶቻችንን የዘጋነው ራሳችን ነን። የአባቶቻችንን የእውነትና የሀቅ መንገድ ስተን ፖለቲከኞቻችን በሰጡን የእኔነት መንገድ ላይ የቆምነው ባልገባን እውቀት ነው።

የምክክር ጽንሰ ሃሳብ በየትኛውም ሀገርና ባህል ውስጥ አንድ አይነት ነው፤እርሱም መግባባትን መፍጠር ነው። ዓለም ላይ በእንዲህ አይነቱ የምክክር ዘዴ ሀገራቸውን ከተጣመመችበት ያቃኑ ብዙ ናቸው። አይደለም ሰው ከሰው፣ አይደለም ፖለቲከኛ ከፖለቲከኛ ቀርቶ በአንድ ልብና አእምሮ እየተመራ እንኳን እግር ከእግርም ይጋጫል።

ትልቁ እና ሊሰመርበት የሚገባው ነገር ያደናቀፈን እንቅፋት መልሶ እንዳያደናቅፈን ከመንገዳችን ላይ ገለል ማድረግ ነው። የእኛ ችግር እንቅፋቱን ከመንገዳችን ላይ ሳናነሳ አንድ ጊዜ ባደናቀፈን እንቅፋት ደጋግመን መደናቀፋችን ነው። ለጦርነት እና ለመለያየት እየዳረጉን ያሉ ችግሮችን መለስ ብለን ብናይ አንድ አይነት ሆነው እናገኛቸዋለን። ሌላው ቢቀር ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ውስጥ የብሄር እሳቤ እያራመድን ያለነው ፖለቲከኞቻችን በፈጠሩት የሀሰት ትርክት ነው።

ከትናንት እስከዛሬ ፖለቲካችን መደናቀፊያችን ነው። ከድሮ እስከ ዘንድሮ የብሄር ጉዳይ መነታረኪያችን ነው። መንገዳችንን ማጥራት አለብን። ስናልፍና ስናገድም በአንድ አይነት መንገድ ላይ በአንድ አይነት እንቅፋት መመታታችን እንዲቀር በእንቅፋቶቻችን ላይ ለውይይት መቀመጥ መፍትሔ የሚሰጠን መላ ነው።

> እስከዛሬ ተወያይተን መፍትሔ ያላመጣነው በችግሮቻችን ስለተበለጥን ነው። በችግር መበለጥ ልክ እንደ እኛ በአንድ አይነት እንቅፋት፣ በአንድ አይነት መንገድ ላይ ደጋግሞ መውደቅ ነው። ከችግሮቻችን የላቀ ሁሉን አቀፍ የለውጥና የተሀድሶ ተራማጅ እሳቤ ያስፈልገናል

ፖለቲካችን እንዳያደናቅፈን፣ ያልኖርነው ትናንትና እንዳያቀያይመን በእውቀትና በሥርዓት የተመራ የተሀድሶ ንቅናቄ ያሻናል። ንቅናቄው የሚጀምረው በአዲስ ሃሳብ ነው። አዲስ ሃሳብ የአዲስ መላ፣ የአዲስ መፍትሔ አብራክ ነው። እስከዛሬ ባልታደሰ ሃሳብ ለውይይት ተቀምጠን ለውጥ ሳናመጣ ቀርተናል።

የምንወያየው ለለውጥ ነው። ያደናቀፉን እንቅፋቶች ዳግም እንዳይጥሉን እንዴት ከመንገዳችን ላይ ገለል እናደርጋቸው የሚል ምክረ ሃሳብን ለማዋጣት ነው። በተዋጣና በታመነበት ሕዝባዊ ተሳትፎ በእንቅፋቶቻችን ላይ ስንወያይ ብቻ ነው መንገዳችንን ከጋሬጣ የምንጠብቀው።

ለችግሮቻችን የመፍትሔ ሃሳብ ከሌለን ያ መንገድ፣ ያፖለቲካ፣ ያ እንቅፋት እንዲያደናቅፈን ፈቅደናል እንደማለት ነው። አሁን ላለችው ኢትዮጵያና አሁን ላለው ሀገራዊ ተግዳሮት ከችግሮቻችን የሚበልጥ የመፍትሔ ሃሳብ ነው የሚያስፈልገን። ከችግሮቻችን በሚበልጥ የመፍትሔ ሃሳብ ነው ፖለቲካችንም ሆነ ሌሎች ነውሮቻችን የሚታከሙት።

እስከዛሬ ተወያይተን መፍትሔ ያላመጣነው በችግሮቻችን ስለተበለጥን ነው። በችግር መበለጥ ልክ እንደ እኛ በአንድ አይነት እንቅፋት፣ በአንድ አይነት መንገድ ላይ ደጋግሞ መውደቅ ነው። ከችግሮቻችን የላቀ ሁሉን አቀፍ የለውጥና የተሀድሶ ተራማጅ እሳቤ ያስፈልገናል።

ብሄራዊ ምክክር ደግሞ ብሄራዊ ተሀድሶን የሚሰጠን የአዲስ ለውጥ ንቅናቄ ነው። እንቅፋቶቻችን በዛ መድረክ ላይ በሃሳብ የበላይነት ተኮርኩመው ተነቃንቀው መውደቅ አለባቸው። ከዛም ከዚም የመጡ አሁናዊና ድሮአዊ ነውጥ ፈጣሪ ተግዳሮቶች እንደ ልብስ በሃሳብ ሳሙና ታጥበው መጥራት አለባቸው።

ሃሳባችን ነውራችንን ካላጠራልን በምንም አንጠራም። ፍቅራችን እድፋችንን ካላጸዳልን ምንም አንጸዳም። እንደሕዝብ ለምክክር ስንቀመጥ እንዴትም፣ ከየትም ይምጡ በችግሮቻችን ላይ የበላይ ለመሆን ነው። ከፊታችን ያለው ሀገራዊ ምክክር ትኩሳቶቻችን የሚሽሩበት የብዙዎቻችን የትንሳኤ ጣይ የሚወጣበት የተስፋ ምስራቅ ነው።

ብሄራዊ ምክክር ለብሄራዊ ተግባቦት እንደ አንድ የዋርካ ስር ነው። ዛፍ በስሩ እንደሚጸና ሀገርም በሃሳብ ነው የምትጸናው። ሃሳብ ግን አይነት አለው። ሀገር የማጽናቱን ያክል ሀገር የሚያፈርሱ ሃሳቦች አሉ። ዓላማችን ሀገር ማጽናት፣ ብሄራዊ አንድነትን ማምጣት እስከሆነ ድረስ በስሮቹ እንደጸናው ዛፍ በዜጎቿ ሃሳብ የጸናች ሀገር ታስፈልገናለች።

ዛፍ ስር ከሌለው ግንድና ቅርንጫፉ፣ አበባና ፍሬው ምንም ነው። ልክ እንደዚህ ሁሉ ሀገር አስታራቂና አንቂ፣ አስማሚ ሃሳብ ከሌላት አበባና ፍሬ፣ ቅርንጫፍና ግንድ እንደሌለው የይስሙላ ዛፍ ናት። የዚህ ውጤቱ ደግሞ በፖለቲካ እንቅፋት መደነቃቀፍ፣ ባልተኖረ ትናንትና ባልመጣ ነገ መባላት የመሳሰሉት ነውሮች ናቸው።

እንደ ሀገር ወደራቀ ነገ ለመዝለቅ፣ አብሮ እንደመጣ፣ አብሮ እንደኖረ፣ አብሮ እንደተዋለደ ሕዝብ የጋራ ሀገርና የጋራ ታሪክ ለመሰነድ በተረት ሳይሆን በእውነት፣ በብሄር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ፖለቲካና ፖለቲከኛ፣ ዜጋና ትውልድ፣ ምሁርና አስተማሪ፣ አንቂና አስታራቂ ያሻናል።

ኢትዮጵያን የሚያሸር፣ የሚታደግ፣ የሚደግፍ፣ የሚለውጥ ሃሳብ ከብሄራዊ ምክክር ተሳታፊዎች ትጠብቃለች። ትውልዱ አንድነቱን ጠብቆ የጋራ ሀገሩን በጋራ እንዲያለማ አባቶቹን የሚያስታውስ ዝክረ አድዋን የመሰለ የአንድነት አውድ ያስፈልገዋል። እንዲህ በመሰለው መንገድ ላይ ስንራመድ ብቻ ነው ትናንት ያደሙን እንቅፋቶቻችን ዛሬ ላይ እንዳይደግሙን የምናደርገው።

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የመንግሥት ግዥ

## ከጥሬ ገንዘብ ወደ ዲጅታል አሠራር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ለማስገባት በሚደረገው ጥረት አበረታች ለውጦች እየመጡ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። መንግሥት አቅም በፈቀደ መልኩ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዲጅታል ኢትዮጵያን በ2025 ዕውን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል። በቅርቡም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር በጋራ በመሆን የመንግሥት ግዢን ከካሽ ውጪ በዲጅታል መፈጸም የሚያስችል የአገልግሎት ካርድ ይፋ አድርገዋል።

ማንኛውንም የመንግሥት ግዢ ከጥሬ ገንዘብ /ከካሽ/ ውጭ መፈጸም የሚያስችለው የግዢ ካርድ ይፋ በተደረገበት ወቅትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ፤ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝና ሌሎች የዘርፉ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በዚሁ ወቅት እንዳሉት፤ ላለፉት በርካታ ዓመታት ባንኮች ወደ ዲጅታል ሥርዓት ለመግባት ሲያደርጉ የነበረው ጥረት በሚፈለገው መጠን መጓዝ ሳይችል ቆይቷል። ይሁንና በአሁኑ ወቅት መንግሥት ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ጥረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣት ችሏል።

እሳቸው እንዳሉት ፤ የዲጅታል ግብይት ሥርዓትን ለማህበረሰቡ ማለማመድ ለረጅም ጊዜ ፈተና ሆኖ የቆየ ቢሆንም መንግሥት የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂን ተግባራዊ በማድረጉ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከባንኮች ቀድመው ወደ ዲጅታል የገቡ የመንግሥት ተቋማት ነበሩ ያሉት ፕሬዘዳንቱ፤ አሁን ላይ ሁሉም ነገር ዲጅታላይዝ እየሆነ በመምጣቱ ቀልጣፋ፣ ፈጣንና ግልጽ የሆነ አገልግሎት ለህብረተሰቡ መስጠት መቻሉንም አንስተዋል። አገልግሎት በኮር ባንኪንግ ሥርዓት በመተሳሰሩ የሁሉም ቅርንጫፍ ደንበኞች የተሟላ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሆነዋል።

ንግድ ባንክ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በሚሰራው ሥራ በርካታ ለውጦች መመዝገባቸውን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ከአንድ ዓመት አስቀድሞ አንድ ትሪሊዮን መግባት ያልቻለው ዘመናዊ የገንዘብ ዝውውር፣ በአሁኑ ወቅት እየተሻሻለ መምጣቱን ተናግረዋል። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ብቻ ሦስት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት የገንዘብ ልውውጥ መደረጉን አስታውቀዋል። ይህም የባንኩን አጠቃላይ ሀብት ሦስት እጥፍ ሊሆን ትንሽ የቀረው ገንዘብ እንደሆነ ነው ያመላከቱት። በዘመናዊ የገንዘብ ልውውጥ ሥርዓቱ ኤ.ቲ.ኤም፣ ሞባይል ባንኪንግ፣ ፖስት ማሽኖችን፣ ሲቢኢ ብርና ሌሎች በርካታ የዲጅታል ክፍያ አማራጮች ጥቅም ላይ መዋላቸውንም አብራርተዋል።

ባንኩ የሀገሪቱን የክፍያ ሥርዓት ለማዘመን የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማቅለልና በኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ገንቢ ሚና ለመጫወት በከፍተኛ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ እንደሚገኝ የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ በማስቀጠል የክፍያ ሥርዓቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዲጅታል ለማስገባትና ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት ለማርካት የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የዲጅታል ስትራቴጂ ላለፉት ሦስት ዓመታት ሲተገበር መቆየቱን የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር እዮብ ተካልኝ አስታውሰው፣ በዚህም ትርጉም ያለው ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉትለ፤ የዲጅታል ስትራቴጂው ዋና ግብ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ማስገባት ነው፤ ይህም በመንግሥት ካልተመራ በስተቀር በተፈለገው ፍጥነት ሊጓዝ አይችልም። በተለይም በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥት ድርሻ ትልቅ በሆነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት መንግሥት ትልቁ ቀጣሪና ገዢ ነው። ስለዚህ መንግሥት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ትልቅ ድርሻ ተጠቅሞ የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ሥራዎችን በዋናነት ይዞ ይሰራል ።



አቶ አቤ ሳኖ



ዶክተር እዮብ ተካልኝና

መንግሥት ሀገራዊ የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ግቡ እንዲሳካ በትኩረት ሲሠራ ቆይቷል ሲሉ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅትም የገንዘብ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የሠራው ሥራ የዚሁ ሥራ አካል እንደሆነ ጠቅሰዋል። ይፋ የተደረገው የግዢ ሥርዓትም አጠቃላይ የመንግሥት ወጪዎች ዲጅታል በሆነ መንገድ ዝውውር ማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ነው ብለዋል። ለዚህም አስቀድሞ በተቀናጀ መንገድ ‹‹ኢፍ ሚስን›› ተግባራዊ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰው፣ በተጨማሪም የተለያዩ አሰራሮች በየደረጃው ተግባራዊ ሲደረጉ መቆየታቸውን ዶክተር እዮብ አስታውቀዋል።

አሁን ደግሞ በተለያዩ የፖስ ማሽኖችና በኢንተርኔት ባንኪንግ ተቋማት ዲጅታሊ የገንዘብ ዝውውር ማድረግ እንዲችሉ የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ መደረጉን ነው የገለጹት። እሳቸው እንዳሉት፤ ግዢ የሚፈጽም አንድ ባለሙያ ካሽ ተሸክሞ መሄድና ባንክ ሄዶ ጥሬ ብር ከባንክ ማውጣት ሳይሆን እንደ ሌሎች ዘመናዊ ሀገራት ካርድ ይዞ በካርድ ግዢ መፈጸም ይችላል። ይህ የግዢ ሥርዓትም ግዢው የተፋጠነ፣ የተሳለጠና ግልጽ እንዲሆን ያደርገዋል።

በአሁኑ ወቅትም ይህንኑ ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ተቋማት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ተቋማቱ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል። አንዳንድ ተቋማት ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በፍጥነት ተግባራዊ እያደረጉ መሆናቸውን አመልክተው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ገና ወደ ዲጅታል ሥርዓቱ እየገቡ እንደሆነ ነው የተናገሩት።

‹‹በመንግሥት የተያዘው አቅጣጫ ሁሉም ተቋማት በተሟላ ሁኔታ ወደ ዲጅታል ሥርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ ነው›› ያሉት ዶክተር እዮብ፤ በተለይም የታክስ ክፍያ የነዳጅ ግዢና ሽያጭ በሙሉ ዲጅታል መሆን አለበት ይላሉ። ሀገራት ከካሽ ዝውውር ሙሉ ለሙሉ እየወጡ ባሉበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያም ጥሬ ገንዘብን በካሽ ከማዘዋወር ሙሉ ለሙሉ ወጥታ ወደ ዲጅታል ሥርዓት እንድትገባ ይደረጋል ብለዋል። የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ከፍተኛ ወጪን እንደሚጠይቅ ተናግረው፤ ገንዘቡን ከማተም ጀምሮ፣ የደህንነት ግዢና ወጪውን ማለትም የገንዘብ ዝውውሩን በሚገባ ለመከታተልና ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እንደሆነ ነው የገለጹት። ወደ ዲጅታል ሥርዓት በመግባት የገንዘብ ዝውውርን ከካሽ ውጪ ማድረግ ግን እነዚህን ሁሉ ችግሮች መፍታት ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎቱ ምቹና ቀልጣፋ እንዲሆን ያደርጋል ብለዋል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ምንም ያልነበረውና የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን ሥርዓት አሁን ላይ እየተስፋፋ መጥቷል ያሉት ዶክተር እዮብ፤ ይህም መንግሥት በቁርጠኝነት የዲጅታል ትራንስፎርሜሽን አጀንዳውን ለማሳካት እየሠራ እንዳለና ከፍተኛ ትኩረት እንደሰጠው አንድ ማሳያ ነው ብለዋል። በቀጣይም ይህን አጠናክሮ በማስቀጠል በሁለተኛው የሪፎርም ምዕራፍ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ዲጅታል ወደ ማድረግ ሥራ ይገባል ነው ያሉት።

በየደረጃው እየተስፋፋ የመጣውን የዲጅታል ግብይት አጠናክሮ በማስቀጠል ሁሉንም የመንግሥት ተቋማት በሰፊው ወደ ዲጅታል ማስገባት በቀጣይ ከሚሠሩ ዋና ዋና ተግባራት መካከል ተጠቃሹ መሆኑን ያነሱት ዶክተር እዮብ፤ በተለይም ከክልሎችና ከፌዴራል መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በክልል የሚገኙ ተቋማትን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱ ማስገባት ቀጣይ የቤት ሥራ እንደሆነ ነው ያነሱት። በመሆኑም ከየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ የሚደረግ የገንዘብ ዝውውርም ሆነ ማንኛውም ግዢ በዲጅታል እንዲሆን ይሠራል ብለዋል።

አሁን ላይ በሁሉም የፌዴራል ተቋማት ዲጅታል ግብይቱን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን እና ካርዱ መዘጋጀቱን የጠቀሱት ዶክተር እዮብ፤ የአገልግሎት ካርዱ በሁሉም የፌዴራል ተቋማት ተደራሽ እንደሚሆንና በቀጣይም ወደ ክልሎች እንደሚወርድ አስታውቀዋል። እስካሁን በተደረገው ግምገማም የዘመናዊ ግብይት ሥርዓቱ ውጤታማ እየሆነ መምጣቱንና ካለው ፍላጎት አንጻር ገና የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በርካታ የዲጅታል አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ እንደቻለ የገለጹት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጅታል ባንኪንግ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ዳዕላክ ይገዙ በበኩላቸው የዲጅታል ዕድገቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ መሆኑን ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ባለፉት ዓመታት በጥቂት ካርዶችና ኤቲኤሞች ተወስኖ አነስተኛ ዕድገት የነበረው ቢሆንም፣ ኢንተርኔት ባንኪንግና ሞባይል ባንኪንግን እንዲሁም ሲቢኢ ብርን እና የተለያዩ የአገልግሎት ካርዶችን አስተዋውቋል። በዚህም ዲጅታል የገንዘብ ዝውውሩ እያደገ መጥቷል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለአብነትም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 64 በመቶ የሚሆነው የባንኩ የገንዘብ እንቅስቃሴ በዲጂታል አማራጮች ማንቀሳቀስ ችሏል። ይህም ማለት 36 የገንዘብ ዝውውር የተካሄደው በቅርንጫፎች ሲሆን፤ ቀሪዎቹ የገንዘብ ዝውውሮች ደግሞ ደንበኞች ባደረጉት የዲጅታል ቻናሎች አማካኝነት ነው። ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ በዲጅታል የገንዘብ ልውውጥ ከፍተኛ ለውጥ እየመጣ ይገኛል። ለተመዘገበው ዕድገትም መንግሥት ያስቀመጠው የዲጅታል አቅጣጫ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በተለይም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ክፍያዎቻቸውን በዲጅታል ክፍያ እንዲፈጸም መደረጉ ለተመዘገበው ዕድገት ጉልህ ድርሻ አለው ያሉት አቶ ዳዕላክ፤ የዲጅታል ዝውውር ዕድገቱ እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ከፍ ያለ እንደሆነ ነው ያስረዱት፤ እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገንዘብ ዝውውር የሚያደርግባቸው ሁለት መንገዶች ያሉት ሲሆን፤ አንደኛው በቅርንጫፎች አማካኝነት ነው፤ ሌላው ደግሞ ዲጅታል ቻናሎች ናቸው። ዲጅታል ቻናሎች በርካታ ሲሆኑ፣ ሞባይል ባንኪንግ፣ ኢንተርኔት ባንኪንግ፣ ኤቲየም፣ ፖስ ማሽን እና ሲቢ ብር የሚባሉ ናቸው።

ባንኩ ከመንግሥት ስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር ጎን ለጎን እየሄደ ያለ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዕላክ፤ መንግሥት ጥሬ ገንዘብን ማተም እስካላቆመ ድረስ ከካሽ ውጪ እንሆናለን ማለት የማይቻልና የካሽ ግብይት የሚቀጠል እንደሆነ ገልጸው፣ ዓለም ላይም ከካሽ ነጻ የሆነ ሀገር እንደሌለም ተናግረዋል። ነገር ግን አማራጭ ካላጣ በስተቀር ካሽን የማይጠቀም ማኅበረሰብ ለመፍጠር ባንኩ አቅዶ እየሠራ ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ባለው ሁኔታም ባንኩ ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን ይፋ ያደረገው የመንግሥት የግዢ ካርድ የዲጅታል ሥርዓቱን ማሳለጥ ይቻላል፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሠራተኞች ደመወዝን ጨምሮ ትላልቅ ክፍያዎችን የሚፈጽም እንደመሆኑ በኢንተርኔት ባንኪንግ ይጠቀማሉ። የዕለት ተዕለት ግዢዎችን በካሽ ወይም ጥሬ ገንዘብ በመጠቀም ይፈጽማሉ። ስለዚህ ይህን ዲጅታላይዝ ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ በመሆኑ ወደዚሁ መግባት ተችሏል። ለዚህም ሥራውን በዋናት የያዘው ገንዘብ ሚኒስቴር ከንግድ ባንክ ጋር በጋራ በመሆን ወደ ዲጅታል ለመቀየር ዝግጅቱን አጠናቅቋል።

በመሆኑም ከዚህ በኋላ ሁሉም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ለሚፈጽሙት ማንኛውም ግዢ ካሽ ወይም ጥሬ ገንዘብ በቼክ የማይንቀሳቀሱ እንደሆነ የገለጹ አቶ ዳዕላክ፤ ለሁሉም መስሪያ ቤቶች ካርዱን ተደራሽ በማድረግ ግዢዎቻቸውን በሙሉ በካርዱ አማካኝነት በዲጅታል የሚፈጽሙ እንደሆነ ነው ያብራሩት። እሳቸው እንዳሉት፤ ሁሉም መስሪያ ቤቶች ኢንተርኔት ባንኪንግ ያላቸው በመሆኑ በየጊዜው የሚፈልጉትን የግዢ መጠን ከኢንተርኔት ባንኪንግ ወደ ካርዱ በመሙላት ግብይታቸውን መፈጸም የሚችሉበት የግዢ ሥርዓት ነው።

ተቋማቱ ካርዱን ለሌሎች ሰዎች አሳልፈው ካልሰጡ በስተቀር በኢንተርኔት ባንኪንግ የሚያደርጉት ግብይት ወይም ክፍያ መጭበርበር የሚገጥመው እንዳልሆነ የጠቀሱት አቶ ዳዕላክ፤ ካርዱ የራሱ የሆነ የደህንነት አካሄዶች እንዳሉት ተናግረዋል። በዚህ በኩል የሚፈጠር ችግር አይኖርም ሲሉም ገልጸዋል። ባንኩ አጠቃላይ ሥርዓቱን እንደሚቆጣጠርና መጭበርበሮች እንደማይፈጠሩ ጠቅሰው፣ በዲጅታል ግብይቱ የሚገጥም ችግር አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

## ‹‹ይቺ ናት ኢትዮጵያ!››

**ዋለልኝ አየለ**

አንዳንድ አገላለጾች በጣም ከመደጋገማቸው የተነሳ የተለመዱ ይሆናሉ። ምናልባትም የተሰለቸ ሁሉ ሊመስል ይችላል። ለምሳሌ በማኅበራዊ የትስስር ገጾች ላይ «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» የሚለው አገላለጽ ለቀልድነት ጭምር እያገለገለ ነው። ብዝሃነትን በተመለከተ ስለሚደጋገም ነው ሰዎች ይህን ቃል ለቀልድነት ጭምር የሚጠቀሙት፤ አሁንስ አበዛችሁት የሚል ሹፈት መሆኑ ነው።

«ይቺ ናት ኢትዮጵያ» የሚለው ግን ገርሞን ሊያበቃ የሚችል አይደለም። በየሄድንበት አካባቢ ሁሉ የምናየው ነገር ካለንበት አካባቢ የተለየ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ አይነትነት የለም። ባህልና ልማዱን፣ የሰዎችን ሥነ ልቦና ካስተዋልን ልዩነቱ ውበት ነው። የምሥራቅ ኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ባህልና ሥነ ልቦና ከምሥራቁ፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ባህልና ሥነ ልቦና ከደቡቡ የተለያየ ነው። አንድ ኢትዮጵያዊ ሀገሩ ውስጥ ብቻ ሀገራትን እንደጎበኘ ሊቆጠር ይችላል።

ይህ ማኅበረሰባዊ ባህልና ሥነ ልቦና በተለያዩ አስተዳደራዊና ውጫዊ ምክንያቶች መጣ እንበል። ከምንም በላይ የሚገርመው ግን በተፈጥሮ ብቻ የተገኙ የተፈጥሮ ብዝሃነቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ የበረዶ ግግርንም የእሳተ ገሞራ ወላፈንንም መጎብኘት ይቻላል። ኩዌትንም አንታርቲካንም እንደ መጎብኘት ማለት ነው። ታዲያ ይህ «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» አያሰኝም?

እነዚህን ሁሉ ነገሮች ያስታወሰኝ ከሰሞኑ ወደ ሰሜን ምሥራቋ አፋር ክልል ያደረኩት ጉዞ ነው። ሌላ ሀገር የሄድኩ እስከሚመስለኝ ድረስ ያየሁት የአየር ንብረት ልዩነት ነው። ወቅቱ የጳጉሜን ወር መሆኑን ረስቼ ግንቦት እና ሚያዚያ ላይ ያለሁ እስከሚመስለኝ ድረስ በላብ መዘፈቄ ነው። አስገራሚ የሚያደርገው ደግሞ የልዩነቱ ቅጽበት ነው።

ጳጉሜን 2 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡00 ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተገኘቻለሁ። ጠዋት ስሄድ የነበረው ዝናብ እና ብርድ የጃኬቴን ኮፍያ አልፎ ይገባል። የበረራ መነሻ ሰዓት እስከሚደርስ ከእግር ጥፍሬ እስከ ራስ ፀጉሬ ተሸፍኜ፣ እሱን አልፎ የሚገባውን ብርድ ለመከላከል እጆቼን እያሻሸሁ ተኮራምቻለሁ።

የበረራ ሰዓት ደረሰና ወደ አውሮፕላኑ ገባን። ወዲያውም በረራው ተጀመረ። ከጎኔ ባለችው መስታዋታማ መስኮት ስመለከት የአዲስ አበባ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ከእኔ በታች ሆነዋል። አንጋጦጬ ሳያቸው የነበሩ አቆልቁዬ አየኋቸው። በአውሮፕላን መሄድ የመጀመሪያዬ ባይሆንም በእንዲህ አይነት መንገድ ባየኋቸው ቁጥር አይኔ አያርፍም። ከከተማው ስንወጣ ደግሞ አረንጓዴው መስክ ተንጣሎ ይታያል። የውሃ ኩሬዎች ነጭ ነጠብጣብ መስለው ይታያሉ።

እንዲህ እንዲህ እያለ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችም፣ አረንጓዴ መስኮችም ሆኑ የውሃ ክምችቶች ከዓይኔ ጠፉ። ከሥር የተረገረገው ደመና ነው። ከበላዬ የነበረው ደመና ከእኔ በታች ሆነ። ጥቅጥቅ ያለ ነጭ ደመና፤ የሰይጣን ጆሮ ይደፈንና አውሮፕላኑ ለማረፍ ቢገደድ ደመናው የሚይዘው ሁሉ ይመስላል። የተነደፈ ጥጥ የመሰለ ነጭ ደመና ከበታቹ ምንም ነገር ያለ አይመስልም። ዳሩ ግን ብዙ አልቆየም፤ ወዲያውኑ ጥቅጥቅ ባለ ጥቁር ደመና ተሸፈነ። በዚህ ሁሉ ውስጥ አንድ ጊዜ ተፈጥሮን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ አውሮፕላንን የሠራ ቴክኖሎጂን እያፈራረቅኩ አደንቃለሁ። አውሮፕላኑ በደመና ምክንያት መሰለኝ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ሲያጋድል ደግሞ ነፍሴ ገርገጭ ትላለች፤ ወዲያውም ብቻዬን ፈገግ እላለሁ።

የበረራ አስተናጋጇ የዕለቱን አብራሪ (ካፕቴን) ካስተዋወቀች በኋላ ያለንበትን ከፍታ፣ የአየር ንብረቱን፣ የምንደርስበትን ሰዓት ነገረችን። አውሮፕላኑ አሁን በአፋር ሰማይ ላይ ነው። ከመነሻ አካባቢ ሳየው የነበረው የመሬት ላይ ነገሮች አሁን መታየት ጀመሩ።

አሁን ግን ሌላ መሬት ነው። ሌላ ተፈጥሮ ነው። ሌላ ወቅት የአየር ንብረት ነው። ያ አረንጓዴ ብርድ ልብስ የተነጠፈበት የመሰለው መሬት አሁን የለም። እነዚያ የውሃ ነጠብጣቦች የሉም። የሚታየው ደረቅ መሬት ነው። የሚታዩት ትንንሽ የበረሃ ቁጥቋጦዎች ናቸው። የአዋሽ ወንዝ ነው የተባለ አንድ ወንዝ ዳርቻ ላይ ግን አረንጓዴ ነገሮችን አስተዋልኩ፤ የመስኖ ውጤቶችም አሉ።

እንዲህ እንዲህ እያለ አውሮፕላኑ ሠመራ ሱልጣን አሊሚራህ ሀንፋሬ አየር ማረፊያ ደረሰ። መሬት ነካ፤ አኮበኮበ፤ ሙሉ በሙሉ ቆመ። የመውጫ በሩ ተከፈተ። ተራዬን ጠብቄ በሩ ላይ ደረስኩ። ልክ አንገቴ ከአውሮፕላኑ በር ሲወጣ እሳት የሚተፋ ነፋስ ፊቴን ገረፈው። ያ ከደቂቃዎች በፊት በብርድ ሲቃጠል የነበረ ፊት በእሳታማ ነፋስ ይገረፍ ጀመር። ከደቂቃዎች በፊት ጃኬቴ አልበቃኝ ብሎ የነበርኩት ሰው ቲሸርቴም በዛብኝ። ወዲያውኑ ወደተዘጋጀው ተሽከርካሪ ውስጥ ገባን። እዚህ ላይ አንድ ያስተዋልኩት ነገር በቆየሁባቸው ሁለት ቀናት ሁሉ የማያቸው የተቋማት ተሽከርካሪዎች ዘመናዊ መሆናቸው ነው። የሙቀት መቆጣጠሪያ (AC) ያላቸው ናቸው፤ ጽዳታቸውን የጠበቁ ናቸው።

ተሽከርካሪው ውስጥ ስገባ በአዲስ አበባ እንደለመድኩት መስኮት ከፈትኩ። በእኔ ቤት እንዳይሞቅ ነፋስ ማስገባቴ ነበር፤ መሆን የነበረበት ለካ እንዳይሞቅ ከውጭ ነፋስ አለማስገባት ነው። የተሽከርካሪው የቅዝቃቄ መቆጠጠሪያ በቂ ነው፤ ነፋስ ከገባ የባሰ ይሞቃል።

በተዘጋጀልን ተሽከርካሪ ለዕለቱ ፕሮግራም ወደተዘጋጀው መድረክ ሄድን። መድረኩ በአፋር ባህላዊ ሙዚቃዎችና ጌጣጌጦች ደምቋል። የሙቀቱ ነገር ግን አልተቻለም። አዲስ አበባ ዝናብ መቶት የነበረው ጫማዬ ርጥበቱ ሳይደርቅ አቧራ ላይ አረፈ። «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» ያልኩት ያኔ ነው። ከደቂቃዎች በፊት ጭቃ የነካው ጫማ ከደቂቃዎች በኋላ አቧራ ላይ አረፈ።

የሙቀቱ ነገር ኃይለኛ መሆኑን ያወቅኩት የእጅ ስልኬ ማስጠንቀቂያ ሲሰጠኝ ነው። ከፍተኛ ሙቀት ስላለ በውስጡ ያሉ መተግበሪያዎች ችግር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ማስጠንቀቂያ ይነግረኛል። የትም ይገቼው ስለማልሄድ ወደ ኪሴ ከተትኩት። ኪሴ ስከተው ደግሞ ሰውነቴን አቃጠለኝ። ያለኝ አማራጭ በእጄ መያዝ ነው።

አፋር ክልል ሞቃት መሆኑን አውቃለሁ፤ ስሄድም የመጀመሪያዬ አይደለም። ከስድስት ዓመታት በፊት ሄጄ ነበር። የተሸወድኩት ግን የአየር ንብረቱን በመሐል ሀገሩ ሁኔታ መገመቴ ነው። ያኔ ስሄድ ወቅቱ የበጋ ወቅት (ታህሳስ) ነበር። የአየሩ ሁኔታ እንደ አሁኑ የከፋ አልነበረም። በበጋ ወቅት እንደዚያ ከሆነ አሁን በክረምት ወቅት በጣም የተሻለ ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ።

ሙቀቱ ያልጠበቅኩትና ያኔ ካየሁት በላይ ሲሆንብኝ ነዋሪዎችን ጠየቅኩ። በክረምት እንዲህ የሆነ በበጋ እንዴት ሊሆን ነው? ብዬ ስጠየቅ በጣም ተገርመው ነው የመለሱልኝ። የበጋ ወቅት ሙቀቱ የሚቀንስበት ነው፤ ምንም እንኳን ኃይለኛ የሚባለው በግንቦት ወር ቢሆንም፤ ከሐምሌ እስከ መስከረም ያለውም ከባድ ሙቀት መሆኑን ነገሩኝ። ከዚያ በኋላ በሆቴልም፣ በባጃጅም በየትኛውም አጋጣሚ ያገኘኋቸውን ሁሉ ስጠይቅ በክረምት ሙቀቱ የሚጠንክርበት ነው። «ከጥቅምት በኋላ እየበረደን ብርድ ልብስ እንለብሳለን» ብለውኛል። ከሐምሌ እስከ መስከረም ግን ለእነርሱም ሙቀት ነው።

ታዲያ ይህ «ይቺ ናት ኢትዮጵያ!» አያሰኝም? ይህ እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። ኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር ናት። ሁሉንም ነገር ያላት ናት። የፈለግነው ነገር ሁሉ የሚገኝባት ናት።

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «ከዳሎል እስከ ዳሽን» የሚባል ፕሮግራም ነበር(አሁን ይኑር አይኑር አላረጋገጥኩም)። ፕሮግራሙ ስለዳሎል እና ሰሜት ተራሮች ብቻ የሚወራበት አይደለም፤ የኢትዮጵያን የብዝሃነት ኃይል ለመግለጽ ነው። በትክክል ገላጭ የሆነ ስያሜ ነው። ይቺ ናት ኢትዮጵያ የሚባለው ለዚህ ነው!

ሌሎቹን አስተውሎቶች ሌላ ቀን እመለስባቸዋለሁ፤

**መልካም አዲስ ዓመት!**

# ዓለም አቀፍ



## የናይሮቢ ስምምነት በኮፕ28 ጉባኤ ለአፍሪካ ድርድር አቋም ሆኖ ይቀርባል

የናይሮቢ ስምምነት በህዳር ለሚካሄደው የኮፕ28 ጉባኤ ለአፍሪካ ድርድር አቋም ሆኖ እንደሚቀርብ ተገለጸ፡፡የመጀመሪያው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ ረቡዕ ሲጠናቀቅ ለአየር ንብረት ለውጥ እርምጃዎች የዓለም መሪዎች ፈንድና ታክስን እንዲደግፉ ጥሪ ቀርቧል። የናይሮቢ ስምምነት የአፍሪካ ሀገራትን ለመርዳት የፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግም ጠይቋል።

ትልቅ ምዕራፍ የሆነው የአፍሪካ የአየር ንብረት ጉባኤ አህጉሪቱ ለአረንጓዴ ኃይድሮጂን ያላትን እምቅ ሀብት በማጉላትና የካርቦን ታክስ ድጋፍን በመጠየቅ በናይሮቢ ስምምነት ተጠናቋል።"ይህ ስምምነት በዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ንግግር ለአፍሪካ የጋራ አቋም መሠረት ሆኖ ያገለግላል" ሲል የስምምነት ሰነዱ ያትታል። አክሎም "የትኛውም ሀገር ከአየር ንብረት ለውጥ እርምጃና ከልማት ለመምረጥ መገደድ የለበትም" ብሏል።

በአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን የሕዝብ ቁጥር ባለው የአህጉሪቱ መሪዎች የተደገፈው ስምምነት፤ በህዳር ለሚካሄደው የኮፕ28 ጉባኤ ለአፍሪካ ድርድር አቋም ሆኖ ይቀርባል።

ዓለም አቀፍ የካርቦን ታክስ እንዲጣል የወተወተው ለሦስት ቀናት የዘለቀው ጉባኤ፤ ግዙፍ ልቀት ያለባቸው ሀገራት ታክስ እንዲከፍሉና ሀብታም ሀገራት ቃል የገቡትን የ100 ቢሊዮን ዶላር ገንዘብ እንዲለቁ ጥሪ አቅርቧል።


የናይሮቢ ስምምነት በነዳጅ፣ አቪየሽንና አየር ትራንስፖርት ላይ የካርቦን ታክስ እንዲጣል የዓለም መሪዎች ይደግፉ መባሉን አል ዐይን ዘግቧል።

## ከልጁ እና ወላጆቹ አንዳቸውን የመምረጥ ግዳታ ውስጥ የገባው ሞሮኳዊ

በፍየል እርባታ የሚተዳደረው ታይብ ኢግንባዝ ከሁለት ልጆቹ፣ ሚስቱ እና ወላጆቹ ጋር በአንድ ግቢ ውስጥ ነበር የሚኖረው፡፡ ሰሞኑን በሞሮኮ በተፈጠረ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ የሟቾች ቁጥር በየጊዜው እያሻቀበ ይገኛል፡፡

ባሳለፍነው ቅዳሜ በተከሰተው አደጋ ተጎጂ ከሆኑ የሞሮኮ ዜጎች መካከል ታይብ ኢግንባዝ አንዱ ሲሆን፤ አደጋው ከተከሰተ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ራሱን ከቤት ፍርስራሾች መካከል ያገኘዋል፡፡ቀሪ ቤተሰቦቹን ሲፈልግ የ11 ዓመት ልጁ እና ወላጆቹ ጎን ለጎን ቤት ተደርምሶባቸው ሲያጣጥሩ ያገኛቸዋል፡፡

በዚህ ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ በሆነበት ቅጽበት ቀድሞ ማንን ማዳን እንዳለበት ግራ ይጋባል፡፡ የግድ መወሰን ነበረበት እና ልጁን ከፍርስራሹ ውስጥ እንዲወጣ ረድቶት እና ተሳክቶለት ወዲያውኑ ወደ ወላጆቹ ሲመለስ ሕይወታቸው አልፎ እንዳገኛቸው ለቢቢሲ በእንባ ታጅቦ ተናግሯል፡፡



ከአደጋው እስከነ ልጁ የተረፈው ሞሮኳዊ

በሞሮኮ የአየር ንብረት ለውጥ "አፈታሪክ" ነው የሚሉ አሉባልታዎች እየተሰራጩ ነው፡፡ እናት እና አባቴ ሕይወታቸው ሲያልፍ በዓይኔ ነው ያየሁት የሚለው ታይብ፤አደጋው እጅግ ሰቅጣጭ እና ልብ ሰባሪ እንደነበር ገልጿል፡፡ወላጆቼን፣ ጥሬ ገንዘቦቼን እና ፍየሎቼን በአደጋው አጥቻለሁ የሚለው የ50 ዓመቱ ታይብ ሕይወትን እንደ አዲስ ሀ ብዬ ለመጀመር ተገድጃለሁ ብሏል፡፡

የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች አሁንም ፍለጋቸውን የቀጠሉ ሲሆን፤ የሟቾች ቁጥር ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ እስከዛሬ ድረስም በአደጋው ሕይወታቸው ያለፉ ዜጎች ቁጥር ከ2 ሺህ 500 በላይ መድረሱን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ሀገሪቱ የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት የአስቸኳይ ጊዜ ከማወጇ ባለፈ ጎረቤት እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሀገራት እና ተቋማት እንዲያግዙ ጥሪ አቅርባለች፡፡

ከአትላስ ተራራ በተጨማሪ በመዲናዋ ራባት፣ በካሳብላንካ እና ኢስዎሪያ የመሬት መንቀጥቀጡ ተሰምቷቸዋል። በተራራማው መንደር የተሠሩ ሕንጻዎች ከመሬት መንቀጥቀጡ የሚተርፉ አይመስልም።በዛ አካባቢ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ ለማወቅም ጊዜ ይወስዳል።

የቢቢሲ ሪፖርተር የመሬት መንቀጥቀጡ በደረሰበት አንድ መንደር ሲደርስ፣ በእድሜ የገፉ ሴት ከአንድ ስፍራ የወጡ 18 አስከሬኖችን እያዩ ሲያለቅሱ ተመልክቷል።ዳግም የመሬት መንቀጥቀጥ ሊኖር ይችላል ብለው የሰጉ በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎች ለሁለተኛ ቀን ከቤታቸው ውጪ ማደር መርጠዋል።

ከፍተኛ የሆነ የምግብ እና የመጠጥ ውሃ እጥረት አለ። የአስቸኳይ ጊዜ የአደጋ ሠራተኞች ከተራራማው አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመድረስ፣ በመሬት መንቀጥቀጡ የፈራረሱ ቤቶች እና ድንጋዮች መንገዱን በመዝጋታቸው አስቸጋሪ አድርጎታል።ይህ ርዕደ መሬት እኤአ በ1960 ከተከሰተው እና የ12 ሺህ ሰዎችን ከገደለው በመቀጠል ከባድ ሆኖ ተመዝግቧል።የተባበሩት መንግሥታት የሞሮኮ ነፍስ አድን ሥራን ለማገዝ ዝግጁ መሆኑን የገለጸ ሲሆን ስፔን፣ እስራኤል እና ፈረንሳይም በተመሳሳይ ቃል ገብተዋል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

# ኢትዮጵያን በቦክስ ያስጠራው በቀለ አለሙ(ጋንች)

ጽጌረዳ ጫንያለው

ብዙዎች «ጋንች» በሚለው ቅፅል ስሙ ያውቁታል። በተለይ የመርካቶ፣ የአውቶቡስ ተራ፣ የአባኮራን ሰፈር ልጆች በዚህ መጠሪያው ነው የሚለዩት። የ82 ዓመት አዛውንቱን በቀለ አለሙን። ቁመተ ለግላጋውን በአካል ለተመለከተው በ60ዎቹ ዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ እንጂ እንዲህ ሰማኒያዎችን የዘለለ አይመስልም።በተለይ ለእንደ እነርሱ አይነት ሰው የማይመከረውን ከበድ ያለ ጭነትን አንስቶ ሲሸከምማ እድሜውን ዋሽቷል የማይል አይኖርም።የዕድሜ ባለጸጋነቱንም መጠራጠሩ የግድ ነው።።

በዙሪያው ያሉ ወጣቶች «ጋሼ» እያሉ ይጠሩታል። ማኅበራዊ ተግባቦቱ ደግሞ ላቅ ያለ ስለሆነ ብዙዎቹ ጋንቺዬ ነው የሚሉት።እናም እኛም አንተ ለማለት የደፈርነው ከዚህ አኳያ ነው።ጋንችን ባለውለታ ነው የሚያሰኘው በርካታ ተሞክሮዎች አሉት።አንዱ በሥራ ወዳድነቱና ጥንካሬው ለብዙ ወጣቶች አርአያ መሆኑ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ በዓለም አደባባይ ሀገሩን በአትሌቲክሱ የአስተዋወቀ የመጀመሪያው የቦክስ ተወዳዳሪ መሆኑ ነው።

ጋንች ስያሜውን ሳይቀር ያገኘው ከጠንካራው የቤት መዝጊያ ቁልፍ ነው።በመርካቶዎች ትልቁ የብረት ቁልፍ ጋንች ይባላልና ለእርሱም ስሙን ሰተውታል። ይህ ቁልፍ በቀላሉ የማይሰበር፣ የማይፈለቀቅና ንብረትን ለሌባ አሳልፎ የማይሰጥ ሲሆን፤ እርሱም በቦክስ ፍልሚያ በተወዳደረባቸው ቦታዎች ሁሉ ማሸነፍ እንጂ እጅ የማይሰጥ ነበር።ጋንች ሌላም ትርጓሜም አለው። በልብስ ላይ የሚተከል ጠንካራ ቁልፍም ነው። ቶሎ ተበጥሶ አይወድቅም። ጋንች መኪናን ለመንተት የሚረዳ የብረት ገመድም ይሆናል። እርሱም ጠንካራ በመሆኑ ከዚህ ጋር ሲያመሳስሉት ስሙን ሰጥተውታል።

ጋንች የትልቅ ጋን ማስቀመጫም የሚል ትርጓሜ አለው። እናም በእግር ኳስ ጨዋታ ውስጥ የመከላከል ተግባሩን ስለሚያከናውኑና ጎል ሳይገባ እንዲያሸንፉ በማድረጋቸው የክለቡ አለኝታ ለማለትም ቅጽል ስሙ እንደወጣለትም በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበረው ቆይታ አጫውቶናል።እንደውም በወጉ መካከልም ቀረብ ብሎ ስለ ጥንካሬው ላነሳበት አንድ የሚለው ነገር አለ።«ልብ ያለው ዛሬም ቢሆን መጥቶ ይግጠመኝ»።

ቦክሰኛው በቀለ አለሙ ( ጋንች) በ1933ዓ.ም በጉራጌ ክስታኔ ውስጥ ከሚገኙ 21 ቀበሌዎች ውስጥ አንዱ በሆነችው የከዝን ቀበሌ የተወለደ ሲሆን፤ አባቱን ገና ልጅ እያለ በሞት አጥቷል።እናቱ ደግሞ ሌላ ትዳር በመመስረታቸው ከቤተሰቡ ጋር መስማማት አልቻለም። ስለዚህም መኖሪያውን ከእናታቸው ወንድ አያት ጋር አደረገ። ይህም እድል ፊቱን አዞረበት።አያቱ ሞቱ። ስለዚህም ሌላ አማራጭ ግድ ነውና ከአያቱ ጋር የአያቱ ልጅ አቶ በዳሶ ጋር ለመኖር አዲስ አበባ መጣ።በአዲስ አበባ አባ ኮራ ሰፈርም ሁለተኛ የእድገት ቦታውን አደረገ።

ጋንች በእራስ እምሩ ግቢ ውስጥ ምርጥ የእግር ኳስ ተጫዋችም ነበር። ከጥንካሬው የተነሳም ብዙ ጊዜ የተከላካይ መስመር ተሰላፊ ነው። የቦክስ ስፖርትም ቢሆን ገና በ16 ዓመቱ ነበር የጀመረው።እነዚህን ሁለት ስፖርቶች ደግሞ ህልሙ ላይ አድርሰውታል።በቀለ የቀለም ትምህርትን መማር የጀመረው በራሱ ጥረት ነው።ቀን እየሰራ በማታው ክፍለ ጊዜ የአስኳላ ትምህርቱን ተከታትሏል።በዚህም በቀድሞ ወሰንሰገድ በአሁኑ የካቲት 23 የመጀመሪያው ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምሯል።ነገር ግን ራሱን ከዚህ በላይ ማስተማር አልቻለም።ከዚያ ይልቅ ልጅነት ህልሙ ላይ መትጋቱን ተያያዘው።

ጋንች የተለያዩ ሥራዎችን ሰርቷል።ጨው ነግዷል፤ የፒያሳው ኅብረት ማኅበር ውስጥ ገብቶም የልብስ ዘምዛሚ ነበረ። ልብስ ሰፊም ሆኖ ያውቃል።ከ1968 ዓ.ም በኋላ የቦክስ ውድድሩን ሲያቆም ደግሞ የመጨረሻውንና እስከለተሞቱ ድረስ ለ50 ዓመታት አሽከርካሪ ነበር[illegible] የታክሲ አገልግሎት በመስጠት ሥራውን አህዱ ያለ ሲሆን፤ ቅጥረኝነቱ ሲሰለቸው ደግሞ የራሱን መኪና ገዝቶ የጭነት አገልግሎት መስጠት ጀመረ።ይህ ደግሞ ለእርሱም ሆነ ለቤተሰቦቹ የገንዘብ አቅም ፈጥሮ እንደነበረ አይረሳውም።ስለዚህም በአቶ በቀለ ያልተነዱ የመኪና አይነቶች ጥቂት ናቸው የሚሉት ወዳጆቹ ለምሳሌ እነ ቼንቶትሬ፣ ፎር አ ፎር የመሳሰሉት መኪኖች በእጁ ገብተው የተሽከረከሩ ነበሩ።



**በሁለቱ ትልልቅ የኦሎምፒክ መድረኮች ላይ አሰልጣኝና የተሟላ ትጥቅ ሳይኖረው ሀገሩን ወክሎ መሳተፍ የቻለው ጋንች፤ በናይጄሪያ ሌጎስ በተካሄደው የአፍሪካ የቦክስ ሻምፒዮን ላይ አሸናፊ በመሆን ሀገሩን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ማስጠራት የቻለ ስፖርተኛ ነው። ቦክሰኛ በቀለ አለሙ በ2004 ዓ.ም የህይወት ታሪኩን የሚዳሰስ —ያልተነገረለት የሀገር ባለውለታ በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መጽሐፍ ታትሞለታል**

### ባለውለታነት እንዴት

ኢትዮጵያን በታላቁ የኦሎምፒክ መድረክ ስሟ እንዲጠራ ያደረጉ ብዙ እንቁ ስፖርተኞች እና አትሌቶች ተፈጥረዋል።ከእነዚህ የሀገር ባለውለታዎች መካከል ደግሞ በቦክሱ ዘርፍ ኢትዮጵያን በኦሎምፒክ መድረክ ለመጀመሪያ ጊዜ የወከለው በቀለ አለሙ (ጋንች) ነው።በቀለ ከ59 ዓመታት በፊት በቶክዮ ኦሎምፒክ ኢትዮጵያን ወክሎ የተሳተፈ ሲሆን፤ ኋላም ተከትለውት ለመጡ የቦክስ ዓለም ሰዎች አርአያና መምህር ሆኗል።ምክንያቱም እርሱ ከቶኪዮ በኋላ በነበሩት የኦሎምፒኮ መድረኮች እና የአፍሪካ ሻምፒዮን ላይ ሀገሩን ወክሎ መሳተፍ የቻለ ፈር ቀዳጅ ስፖርተኛ ስለነበር።።

ጋንች የቦክስ ዓለምን እንዲቀላቀል የሆነው ፊልም አይቶ ሲሆን፤ የአሜሪካው የቦክስ ውድድር የቦክሱን ስልጠና እንዲወስድ አስችሎታል።አቶ እስጢፋኖስ የሚባሉ ኤርትራዊ አሰልጣኝ ደጃች ውቤ ቅጥር ግቢ ውስጥ «አዲስ አበባ ወጣቶች» በሚል ክለብ አደራጅተው የተለያዩ ስፖርታዊ ስልጠናዎችን ይሰጡ ነበርና ከፊልሙ በኋላ በቀጥታ ጊዜ ሳያጠፋ ሄዶ ተመዘገበ። ልብስ ስፌቱን ጎን ለጎን በመስራትም ጉጉቱን ወደ ማርካቱ ገባ።ይሁን እንጂ ሌሎች ልጆችን ያሰለጥን ነበርና ቦክስ ማሰልጠን አትችልም ተብሎ ታገደ።በዚህም ሥራው ተቋረጠ።

ሕልሙን ዝም ብሎ የማይተወው በቀለም ሌላ አማራጭ ፈለገ።እድል ቀናውናም በታዋቂው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ አማካኝነት በተቋቋመው «ዘርአይ ድረስ» ክለብ ውስጥ ገባ። አጋጣሚውም የውድድር ዕድል ከፈተለት።በ1959 ዓ.ም የቅዱስ ጊዮርጊስ እግር ኳስ ክለብን ወክሎም ተወዳደረ።

የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን ሕጋዊ ሰውነት ሲሰጠው ደግሞ በሀገር ደረጃ ተመርጦ በዓለም መድረክ እንዲወዳደር እድሉን አገኘ።ለመጀመሪያ ጊዜ በሪንግ ውስጥ የገጠመው ቦክሰኛ ሰለሞን ዓለም የተባለ ሲሆን፤ ሰውነቱ ጠንካራና ግዙፍ ነበር። በጊዜው ደረቱ ላይ ድንጋይ ቢፈልጡበት የማይሰማ ቦክሰኛ እየተባለ ይሞካሻል።ሆኖም ዕድልና ትጋት ወደ ጋንች አምርታ ድል የእርሱ ሆነች።ይህ ደግሞ ሀገር ወክሎ እንዲወዳደር መንገድ ከፈተለት።በጊዜው ኢትዮጵያን ለመወከል ከሸዋ፣ ከፋና አስመራ የመሳሰሉት ክፍለ ሀገራት ላይ በመወዳደር በነጥብ ማሸነፍ የግድ ይላል። የጋንች ዕጣ ፈንታም ከዚህ የተለየ አልነበረም። እናም ሁሉንም በዝረራ አሸንፎ ተመረጠ።

በሚሊተሪና በግል ከሚሰለጥኑ ቦክሰኞች ጋር ለውድድር ቀርቦ አንድም ቀን ተረቶ አያውቅም።በ1952 ዓ.ም ጋንች በቦክሱ ዘርፍ በሮም ኦሎምፒክ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያን ወክሎ ለመሳተፍ ወደ ጣሊያን ሮም ለማምራት ዝግጅት እያደረገ ባለበት ወቅት ግን በበጀት እጥረት ምክንያት የቦክሰ ቡድኑ መቀነሱን ተከትሎ በውድድሩ ላይ የመካፈል እድሉን ሳያገኝ ቀረ።ይሁን እንጂ ነገም ሌላ ቀን እንደሆነ ያምናልና በሮም ኦሎምፒክ ያጣውን የመሳተፍ እድል ለማግኘት የተሻለ ሥራ መስራቱን ቀጠለ።በግል በመሰልጠን የሸዋ ጠቅላይ ግዛትን ወክሎ ተመረጠ።ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ ኢትዮጵያን ወክሎ ወደ ጃፓን ቶኪዮ ኦሎምፒክ ተጓዘ። በዚህም በተሻለ ስልጠና እና ዝግጅት በኦሎምፒክ ውድድሩ ስኬታማ ሊባል የሚችል ተሳትፎን ማድረግ ቻለ።በውድድር ተሳትፎውም የመጀመሪያ ዙር ላይ ብቃቱን አሳየ።።

በሁለተኛው ዙር ደጋፊዎቹ ነጮች በመሆናቸው ፊላንዳዊውን ለማንቃት ብለው እየጮሁ ተፅዕኖ ፈጠሩበትና ተሸነፈ።ሆኖም ነጭና ጥቁር ሲፈታተሽ የታየበት ጨዋታ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አድናቆታቸውን ቸረውት ነበር። ይህ ደግሞ በትልቁ የዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የኢትዮጵያን ስም ከፍ ያረገበት ነው።በቦክሱ ዘርፍ ሀገሩን ወክሎ በመሳተፍም ፈር ቀዳጅ እና ለብዙ ስፖርተኞች አርአያም የሆነበት ጊዜ ነበር።

ቀጣዩ ጉዞው ወደ ሜክሲኮ የሚወስደው ሲሆን፤ ተስፋ የቆረጠበት ቦታ ነበር።ዋነኛ ምክንያቱ ደግሞ የዘር መድሎ፤ በተለያየ ውዝግብ ውስጥ አልፎ ኦሎምፒክ ላይ ተሳታፊ በመሆኑ ከሜክሲኮ መንግሥት ሜዳሊያዎችን የተቀበለበት ነው።በዚህ ተሳትፎውም ዳግመኛ ሀገሩን ከፍ አድርጓል።

በሁለቱ ትልልቅ የኦሎምፒክ መድረኮች ላይ አሰልጣኝና የተሟላ ትጥቅ ሳይኖረው ሀገሩን ወክሎ መሳተፍ የቻለው ጋንች፤ በናይጄሪያ ሌጎስ በተካሄደው የአፍሪካ የቦክስ ሻምፒዮን ላይ አሸናፊ በመሆን ሀገሩን በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ማስጠራት የቻለ ስፖርተኛ ነው። ቦክሰኛ በቀለ አለሙ በ2004 ዓ.ም የህይወት ታሪኩን የሚዳሰስ “ያልተነገረለት የሀገር ባለውለታ በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መጽሐፍ ታትሞለታል።


ቦክሰኛ በቀለ በተለይም በወቅቱ በቦክሱ ስማቸው ጎልቶ ይጠራ ከነበሩት ቦክሰኛ ማሞ በየነ፣ ቦክሰኛ አሰፋ ጎሬላ እና ቦክሰኛ ጉዲሳ ሆራ ጋር የሚያደርጋቸው የተለያዩ የቦክስ ውድድሮች ስሙን ይበልጥ ታዋቂ ያደረጉለት ናቸው።እርሱ ከውጭ ሀገር የውድድር ተሳትፎ አልፎም በሀገር ውስጥ በርካታ ውድድሮችን አድርጓል።

የተሻለ ብቃት ያሳየባቸውም በርካታ ውድድሮች አሉ።ከእነዚህ መካከል ግን አንዱ በሁሉም ልብ ውስጥ የማይጠፋው በሲኒማ አዲስ ከተማ የገጠመው ካሜሮናዊ ጉዳይ ነው።ሰውዬው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ቶማስ ፍራንሲስ ሲሆን፤ በአገረ ካሜሮን ለአራት ዓመታት የከባድ ሚዛን ሻምፒዮና ቦክሰኛ ነበር። ግን «ከአቶ በቀለ ጋር መግጠም እፈልጋለሁ» ባለው መሠረት በ1956 ዓ.ም በጋንች ጠንካራ ቡጢዎች ተመትቶ ወድቋል።በወቅቱ «አዲስ ድምጽ» የተሰኘው ጋዜጣ ባሳተመው ጽሑፉ «በቀለ የካሜሮኑን ቡጢኛ በቃኝ አስባለው» በሚል ርዕስ እንደጻፈም የታሪክ መጽሐፉ ያስረዳል።

ጋንች የድሮው ማዘጋጃ ቤት፣ ሞስኮብ ሲኒማ፣ ሀገር ፍቅር ቴአትር፣ ሲኒማ ኢትዮጵያ ፣አደዋ ሲኒማ፣ ራስ ቴአትር፣ ሲኒማ አዲስ ከተማ፣ አምባሳደር ቴአትር፣ ብሔራዊ ቴአትር የመሳሰሉት በዋናነት በሀገር ውስጥ ውድድር ይደርግባቸው የነበሩ ቦታዎች ናቸው።በእነዚህ ቦታዎች በሚዘጋጁ የቦክስ ውድድሮች ላይ በሚሳተፍበት ወቅት ብዙ ደጋፊዎች እንደነበሩት የሚነገር ሲሆን፤ በየሳምንቱ በየሲኒማ ቤቱ በቦክስ አፍቃሪዎች ታጅበው ውድድሮች ሲካሄዱ የበቀለን (ጋንች) ኃይለኝነት ማንም አይረሳውም።በተለይም ግራ ቡጢ ለመመልከት የሚያስችለውን ጥበብ ሲጠቀም ሲኒማ ቤቶች በድጋፍ ይናወጡ ነበር።እርሱ አለ ከተባለም እንዲሁ ሰው በሲኒማ ቤቱ ውስጥ ለመገኘት ይጨናነቅ ነበር።ይህ ደግሞ የሲኒማ ቤቶችን ገቢ ከፍ በማድረግ ሀገር ተጠቃሚ እንድትሆን ያስቻለበት ነው።

በቦክስ ዓለም ከ1949 እስከ 1953 ዓ.ም «በአዲስ አበባ ወጣቶች» ክለብ ሲሰለጥንና ሲወዳደር የቆየው ባለታሪኩ፤ ከክለቡ ምንም ዓይነት ክፍያ አያገኝም ነበር። ለእርሱ ክፍያው እውቅናና ክህሎት ብቻ ነው። ይህ ግን አንድም ቀን ቆጭቶት አያውቅም።ምክንያቱም ሀገሩን ከፍ አድርጎበታል።በዚህም እስከለተሞቱ ድረስ ለሀገሩ በአበረከተው ነገር ደስተኛ ነው።የ11 ልጆች አባት የነበረው ቦክሰኛ በቀለ አለሙ ባደረበት ሕመም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ በ82 ዓመቱ ነሐሴ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ከዚህ ዓለም የተለየ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ሽጎሌ በሚገኘው ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ተፈፅሟል።

# ስፖርት



# ‹‹ሁሌም ከአትሌቶች ጀርባ አለሁ››

- -አትሌት ቀነኒሳ በቀለ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው በዓለም ታሪክም ከታዩ ምርጥ አትሌቶች አንዱ የረጅም ርቀት ንጉሱ ቀነኒሳ በቀለ ነው፡፡ ከመም እስከ ጎዳና ላይ ውድድሮች አስደናቂ ብቃቱን ያስመሰከረው ይህ ድንቅ አትሌት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዙ ውድድሮች እየታየ አይገኝም፡፡ ቀነኒሳ በተጠናቀቀው ዓመት ከተካሄደው የቡዳፔስቱ ዓለም ቻምፒዮና መልስ  ኢትዮጵያን የወከሉ አትሌቶች ጋር በመገኘት የሞራል ድጋፍ ሲያደርግ ነበር፡፡

ውድድሩን ተከትሎም በሰጠው አስተያየት “ጥሩ ውጤት ነው የተገኘው” በዚህም ደስ ብሎኛል፡፡ በተለይ በማራቶንና በ10ሺ ሜትር ሴቶች የተገኘው ውጤት እጅግ አስደሳች ነው፡፡ እንዳየነው በእልህ አስጨራሽ ፉክክር ይህ ውጤት መገኘቱ አመርቂ ሊባል የሚችል ነው፡፡ ሆኖም በአንዳንድ ተጠባቂ ርቀቶች ውጤት ባለመገኘቱ ተሰምቶኛል፡፡ በልምድ፣ የአቅምና በቴክኒክ ማነስ ይህ ሊሆን እንደቻለ እገነዘባለሁ፤ አንዳንዶቹ ግን አቅም እያላቸው ውጤት የታጣባቸው ርቀቶች አሉ፡፡ በእነዚህም ላይ ለወደፊቱ አትሌቶችን በሥነልቦና በማጠናከር ወደ ውድድር እንዲገቡ እንዲሁም የተፎካካሪ አትሌቶችን ደካማ ጎን በማውጣት ምክር ቢሰጥ ይሻሻላል ብዬ አስባለሁ›› ብሏል፡፡

ቀነኒሳ በመም ውድድሮች ላይ በርካታ አስደናቂ ገድሎችን ፈፅሟል፣ እሱ የበላይነቱን ለረጅም ጊዜ በተቆጣጠረበት የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች አሁን ያለው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤት እየቀነሰ



በመምጣቱ ይቆጫል፡፡ ምክንያቱን ሲገልጽም ‹‹ውጤት የጠፋው ጠንካራ አትሌቶች ስለሌሉ አይደለም፡፡ በእርግጥ በአንዴ አትሌቶችን ማግኘት አይቻልም ነገር ግን ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ ነው፡፡ የታዳጊ ፕሮጀክቶች እና ወጣቶች ላይ ከተሠራ ውጤቱ ይመለሳል የሚል እምነት አለኝ›› ይላል፡፡

ባለፉት የዓለም ቻምፒዮና እና ኦሊምፒኮች በተለይ በኃይሌ ገብረስላሴ፣ በቀነኒሳ በቀለ እና ስለሺ ስህን የቡድን ቅንጅት የተገኙት ሜዳሊያዎች ከኢትዮጵያውያን ትውስታ ሊሰረዙ የማይችሉ ናቸው፡፡ በአንጻሩ አሁን ላይ ያሉት አትሌቶች እንደቀድሞው አለመሆናቸው ይስተዋላል፡፡ በዚህ ላይም ጠንካራው አትሌት ‹‹በቡድን ለመሥራት ጥረት ያደርጋሉ፤ ሆኖም ይህም ራሱን የቻለ ችሎታ ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል በኡጋንዳውና በእኛ አትሌቶች መካከል ያለው የብቃት ደረጃ የሚለያይ ነው፤ ስለዚህም ጠንካራ ሥራ ይፈልጋል፡፡ ጊዜው በሄደ ቁጥር ሁኔታዎችም መለወጣቸው አይቀርም። በሁለቱም ርቀቶች ከ15 ዓመት በፊት ክብረወሰኑ የእኛ ነበር፡፡ በሂደትም ነገሮች ዘመናዊ መልክ እየያዙ፣ ጠንካራ አትሌቶች እየተፈጠሩ ክብረወሰኑም ሊሻሻል ችሏል፡፡ ነገር ግን ይህንን ክብር ወደ ሀገሩ ሊያስመልስ የሚችል ብቃት ላይ የሚገኝ አትሌት ማፍራት የግድ ነው፡፡ በመሆኑም ተፎካካሪው አትሌት ጠንክሮ በመሥራት አሸናፊ እንደሆነ በመረዳት የእኛ አትሌቶችም በቁጭት ሊሠሩ ይገባል፡፡ አሁን ላይ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ የስፖርት ትጥቆች በተለይ የመሮጫ ጫማዎች ፍጥነትን በመጨመር ሰከንዶችን ሊያፈጥኑ የሚችሉ መሆናቸው የአትሌቱን ብቃት ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡ በዚህ በመታገዝ እንዲሁም በጠንካራ ሥራ ውጤታማ መሆን ይቻላል፤ የተወሰደብን ክብረወሰንም አንድ ቀን እንደሚመለስ ተስፋ አደርጋለሁ›› ሲል ያብራራል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከአትሌቶች ዝግጅት ጎን ለጎን እነ ቀነኒሳን የመሰሉ የዓለም የምንጊዜም ምርጥ አትሌቶች አጋርነት ሁሌም አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው፡፡ መጪው ኦሊምፒክ እንደመሆኑም በቻምፒዮናው የታየው ሁኔታ እንዳይደገም ከአንጋፋ አትሌቶች ምን ይጠበቃል? ‹‹እኔ ለአትሌቶች ልምዴንና ምክሬን እንዳካፍል በፌዴሬሽኑም ተጋብዣለሁ፡፡ ነገር ግን በግሌም ቅርበት ካለኝ አትሌቶች ጋር ምክር ከመስጠት ባለፈ ባገኘሁት አጋጣሚ በልምምድ ቦታም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮ ስንገናኝ ልምዴን ሳካፍል ነው የቆየሁት፡፡ ሁሌም ከአትሌቶች ጀርባ ነበርኩ በቀጣይም መሰል አስተዋጽኦዬን የምቀጥል ይሆናል›› ብሏል፡፡

በሌላ በኩል ‹‹አትሌቶች ልምምድ ሊያደርጉበት የሚችሉበትን መም በመገንባት ወጣቶች እንዲበራከቱ እገዛ እያደረኩ ነው፡፡ በሱሉልታ አካባቢ መም በመገንባቴ በርካታ አትሌቶች እየተጠቀሙበት ነው፡፡ ይህንን ያደረኩት ወጣት አትሌቶችን ከማገዝ ጎን ለጎን የሚወደኝን ሕዝብ ለማስደሰትም ነው፡፡ የተለያዩ የንግድ አማራጮች ላይ በመሳተፍ ገቢ ማግኘት ብችልም ትኩረቴን ስፖርቱ ላይ በማድረግ ለሀገር ውጤት የሚመዘገብበትን መንገድ ለመፍጠር በማሰብ ነው፡፡ በእርግጥም በርካታ አትሌቶች እየሠሩበት ነው፤ ውጤታማም ሆነዋል››፡፡

በማራቶን የዓለም ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት ባለቤት የሆነው ቀነኒሳ የማራቶን ክብሩን ወደ ኢትዮጵያ ያስመልሳል የሚለው የበርካቶች ዕምነትና ምኞት ነው፡፡ ይህ መቼ ሊሳካ ይችላል የሚለውንም ‹‹በእርግጥ ይህ ሰዓት እንደቀላል የሚታይ አይደለም፤ ፈጣን ሰዓቶች በየጊዜው እየተመዘገቡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን እኔም ውድድር አላቆምኩም፤ እስካሁንም ክብረወሰኑን ለመስበር የቀሩኝን 2ሰከንዶች ለማሻሻል የያዘኝ የእግሬ ሕመም ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ግን ጥረቴን እቀጥላለሁ፤ እኔ ባልችልም የሀገሬን ልጆች በመደገፍ ክብረወሰኑ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ የቻልኩትን ሁሉ አደርጋለሁ›› ሲል አብራርቷል፡፡


## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከተማ ክ/ከ ወረዳ 12 የቤት ቁጥር 007/መ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0041548247 ኤልያስ መንገሻ ትባ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ገቢዎች ሚ/ር አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተርን አቨር ታክስ /ቲኦቲ/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 0050 የተሰራበት  ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም  ኤልያስ መንገሻ ትባ**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0002415848 ብርሃኔ እስጢፋኖስ ጨፍቅ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ቢሮ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተርን አቨር ታክስ /ቲኦቲ/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 0350 የተሰራበት እና ከ0351 እስከ 500 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ቢሮ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም  ብርሃኔ እስጢፋኖስ ጨፍቅ**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ/f2-004/051 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0003257420 ሣላሀዲን መለስ ወልደማርያም በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ማሽን ገዝቼ ስራ መስራቴን ይታወሳል በመሆኑም ከማሽን የተቆረጠ ደረሰኝ  FSNo ከቁጥር 185 እስከ 190 ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም  ሣላሀዲን መለስ ወልደማርያም**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 482/483/B301  ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0067256536 ከድር አህመድ ሰይድ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ቢሮ የካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር 001 እስከ 006 የተሰራበት  እና ከቁጥር 007 እስከ 0050 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ቢሮ የካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም  ከድር አህመድ ሰይድ**